# እርካብ

## የሬዲዮ ፕሮግራም

## የአድማጮች ቡድን ውይይት መመሪያ


የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Health

USAID
FROM THE AMERICAN PEOPLE

JOHNS HOPKINS
Center for Communication Programs

JSI

# እርካብ የራዲዮ ድራማ
## የአድማጮች የቡድን ውይይት መመሪያ

ይህ ሰነድ የተዘጋጀው የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች እንዲሁም ሌሎች በማህበረሰብ ጤና ዙሪያ የሚሠሩ ሰዎች እርካብ ተከታታይ የራዲዮ ድራማን ተጠቅመው የአድማጮች ቡድኖች ለማደራጀት እና ውይይት ለመምራት እንዲያግዛቸው ነው። ይህ የውይይት መመሪያ የሚያገለግለው ለራዲዮ ድራማው ከ1-12 ላሉት ክፍሎች ነው።

# ማውጫ

## ወደ እርካብ እንኳን በደህና መጡ


የአወያዩ ሚና 2

አወያዮች ሊያደርጓቸው የሚገቡ እና ማድረግ የሌለባቸው ነገሮች 5

የዚህ መመሪያ አጠቃቀም 6

ለእርካብ የራዲዮ ድራማ የአድማጮች ቡድን ማቋቋም 7

የውይይቱ መመሪያዎች የሚተገበሩበት አጠቃላይ አካሄድ 9


## በተውኔት ላይ የሚደረግ ውይይት መመሪያዎች


ክፍል 1፦ በጫና የሚፈፀም ጋብቻ 12

ክፍል 2፦ አዳዲስ ጅምሮች 16

ክፍል 3፦ በባልና ሚስት መካከል የሚደረግ ግልፅ ውይይት 20

ክፍል 4፦ ከቤተሰብ እቅድ ጋር በተያያዘ የወንዶች ተሳትፎ 24

ክፍል 5፦ የጋራ ችግሮችን ለመፍታት የማኅበረሰብ ተሳትፎ 28

ክፍል 6፦ በባልና ሚስት መካከል ያለ የኃይል ሚዛን 32

ክፍል 7፦ የተለምዶ ሕክምና 36

ክፍል 8፦ በፆታ ላይ የተመሠረተ ጥቃት 40

ክፍል 9፦ የወባ በሽታ ሕክምና ማግኘት 44

ክፍል 10፦ አጎበር መጠቀም 48

ክፍል 11፦ ስለ ቤተሰብ ዕቅድ የተሳሳተ አመለካከት 52

ክፍል 12፦ ቅድመ ወሊድ ክትትል ቶሎ መጀመር 56

# ወደ እርካብ እንኳን በደህና መጡ

እርካብ አዝናኝ የሆነ ተከታታይ የራዲዮ ድራማ ነው። ድራማው አድማጮች የራሳቸውን ህይወት እንዲቃኙ እና ይበልጥ ጤናማ የሆነ አኗኗር እንዲከተሉ ተብሎ የተዘጋጀ ነው። በራዲዮ ድራማው ሰዎች የተለያዩ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችሏቸውን ባህሪያት እንዲያዳብሩ፣ በባልና ሚስት መካከል ግልፅ ውይይት እንዲኖር፣ አጠቃላይ የሥርዓተ ፆታ ግንኙነቶች እንዲሻሻሉ እና ሌሎች ጤና ላይ ተፅዕኖ ያላቸው ማኅበራዊ ጉዳዮች እንዲሻሻሉ የሚያግዙ በርካታ ርዕሶች ተካትተዋል።

ይህ የውይይት መመሪያ የተዘጋጀው ለእርካብ ራዲዮ ድራማ የአድማጮች ቡድን አወያዮች ነው። የአድማጮች ቡድን አወያዮች አድማጮች በድራማው ላይ የተነሱትን ጉዳዮች አስተውለው የራሳቸውን ህይወት እንዲመረምሩ በመርዳት ረገድ ጉልህ ሚና ይጫወታሉ።

# የአወያዩ ሚና

አወያዮች ድራማው ላይ የተነሱት ጉዳዮች አድማጮች እንዲረዱና ጉዳዩን ከራሳቸው ህይወት ጋር በማነፃፀር እንዲማሩ ይረዳሉ። ማወያየት እና ማስተማር የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውን ማስታወስ አስፈላጊ ነው። አወያይ ሲሆኑ ያለብዎት ኃላፊነት አድማጮች ድራማውን ከተከታተሉ በኋላ የራሳቸውን ሕይወት ማጤን በሚችሉበት መልኩ ውይይቱን መምራት ነው። አድማጮች ምንም ሳይሸማቀቁ፣ በነፃነት የግል ተሞክሯቸውን ማካፈልና አዳዲስ ሐሳቦችን ማፍለቅ ከቻሉ እንዲሁም በመካከላቸው የመተማመን እና የመከባበር መንፈስ ከሰፈነ የሚያደርጉት ውይይት እጅግ ፍሬያማ ይሆናል። ይህ እንዲሆን አወያዮች የሚከተሉትን ጨምሮ አንዳንድ ወሳኝ የሆኑ ባሕርያት ሊኖሯቸው ይገባል፦

- የተሳታፊዎችን ፍላጎት ማስተዋልና መረዳት
- ትችት ለመቀበልና ለመማር ዝግጁ መሆን
- ከአድልዎ በመራቅ ሁሉም ተሳታፊዎች ሃሳባቸው እንዲደመጥ እና አመለካከታቸው እንዲከበር ማድረግ

ውይይቱን መምራት ከመጀመርዎ በፊት በቂ ዝግጅትና ልምምድ በማድረግ እነዚህን ባሕርያት ማዳበር ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ ጥሩ ችሎታ ያላቸው አወያዮች ለሚከተሉት ነጥቦች ትኩረት ይሰጣሉ።

## አካላዊ ገለፃ

የአካል ገለፃዎች ለታዳሚዎች የሚያስተላልፉት መልእክት አለ። መልካም የፊት ገፅታ በማሳየት፣ ፈገግ በማለትና አግባብ የሆኑ የእጅ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ እና ሌሎች ተገቢ አካላዊ መግለጫዎችን በመጠቀም አድማጮች ሐሳባቸውን እንዲገልጹ ማበረታታት ይኖርብዎታል። ሆኖም አካላዊ ገለፃዎች የአድማጮችን ትኩረት እንዳይከፋፍሉ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ሰዎች በሚናገሩበት ጊዜ ጀርባዎን አይስጡ። ከዚህም ሌላ ውይይቱ በሚደረግበት ጊዜ አስተማሪ እንዳይመስሉ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብዎታል። ለምሳሌ፣ ታዳሚዎች ተቀምጠው እያለ እርስዎ ፊት ለፊታቸው የሚቆሙ ከሆነ ከእነርሱ ጋር ያለዎት ግንኙነት የአስተማሪና የተማሪ ሊመስልና ውይይቱም በዚያው መልክ ሊወሰን ይችላል። ስለዚህ ከታዳሚዎቹ ጋር አብረው ቢቀመጡ ይመረጣል። ታዳሚዎቹ በተቻለ መጠን በነፃነት እንዲናገሩ ይፍቀዱላቸው።

## በታዳሚዎች መካከል የሚታይ ልዩነት

ሰዎች በቡድን ወይም በስብሰባ ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ ከተለመደው የተለየ ባሕሪይ ሊያሳዩ ይችላሉ። አንዳንዶች ውይይቱን የሚቆጣጠሩት ሲሆን ሌሎች ደግሞ ሐሳባቸውን መግለጽ ሊያሳፍራቸው ይችላል። አወያይ እንደመሆንዎ መጠን ሁሉም ተሳታፊዎች ሐሳባቸውን እንዲገልፁ እኩል አጋጣሚ መፍጠር አለብዎት። በአንድ በኩል ውይይቱን መቆጣጠር የሚፈልጉ ሰዎች ለሌሎች የመናገር አጋጣሚ እንዲሰጡ በዘዴ ጣልቃ መግባት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ዓይናፋር የሆኑት እንዲናገሩ ማበረታታት አለብዎት።

**ግልጽ መሆን**

ሐሳብዎን ተሳታፊዎች ሊረዱ በሚችሉት ቀለል ባለ መንገድ ይግለጹ፡፡ ታዳሚዎች ላይረዷቸው የሚችሉ ውስብስብ የሆኑ የሕክምና ወይም ሙያዊ ቃላትን አይጠቀሙ፡፡

**አዎ/አይ የሚል መልስ ያላቸውን ጥያቄዎች በተቻለ መጠን አለመጠቀም**

ክፍት የሆኑና ማብራሪያ የሚጠይቁ ጥያቄዎች ማቅረብ ውይይቱ ይበልጥ ትርጉም ያለው እንዲሆን ያስችላል፡፡ አዎ ወይም አይ የሚል መልስ የሚሰጥባቸው ጥያቄዎች ሐሳቦች እንዳይንሸራሸሩ በማድረግ ውይይቱን ይገድባሉ፡፡

**በንቃት መከታተል**

አወያዮች የመግባባት ችሎታ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ኃበዝ አወያዮች ጥሩ አዳማጮች ናቸው፡፡ ተሳታፊዎች ሲናገሩ በትኩረት ማዳመጥ፣ ውይይቱ ወዴት እያመራ መሆኑን ማስተዋል እና ሁሉም ሰው ሊረዳው የሚችል ቋንቋ መጠቀም ጥሩ አወያዮች ያሏቸው ወሳኝ የመግባባት ክህሎቶች ናቸው፡፡

**መዘጋጀት**

ጥሩ አወያዮች አስቀድመው እቅድ ያወጣሉ፡፡ እቅድ ማውጣት አወያዮች ውይይቱን በልበ ሙሉነት እንዲያካሂዱ የሚረዳ ከመሆኑም በላይ ለሁኔታዎች እንዳስፈላጊነቱ ምላሽ ለመስጠት ያስችላቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አወያዮች የሚያጫውቱትን የድራማ ክፍል፣ ድራማውን የሚያጫውቱበትን ሬዲዮ፣ የውይይቱን መመሪያዎች እና የመሳሰሉ አስፈላጊ ነገሮች አስቀድመው ያዘጋጃሉ፡፡

**የማጠቃለያ ሐሳቦች**

አወያዮች በውይይቱ መጨረሻ ላይ ቁልፍ ነጥቦችን ጨምቀው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ የማጠቃለያ ሐሳብ ላይ ሊቀርቡ የሚችሉ ቁልፍ ነጥቦች በዚህ መመሪያ በእያንዳንዱ ክፍል መጨረሻ ላይ ቀርበዋል፡፡ ይሁን እንጂ መመሪያው ላይ ያልተካተቱ ነገር ግን በውይይቱ ላይ የተነሱ ወሳኝ ነጥቦች ካሉ አብረው ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ እነዚህን ነጥቦች በማጠቃለያው ላይ ማንሳት እንዲችሉ በውይይቱ ወቅት ማስታወሻ ይያዙ፡፡

# አወያዮች ሊያደርጓቸው የሚገቡ እና ማድረግ የሌለባቸው ነገሮች

| ሊያደርጓቸው የሚገቡ | ማድረግ የሌለባቸው |
|---|---|
| ተሳታፊዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ሲገናኙ ራሳቸውን እንዲያስተዋቁ ዕድል መስጠት፤ ቀለል ያሉ የማነቃቂያ ጨዋታዎች ማዘጋጀት | ተሳታፊዎች ሃሳባቸውን በሚገልፁበት ጊዜ አለማቋረጥ፤ ለዚህም እንዲረዳ አንድ ተሳታፊ ተናግሮ ካበቃ በኋላ አምስት ሴኮንድ መጠበቅ |
| የውይይቱን ዓላማ ግልፅ ማድረግ እና ተሳታፊዎች ሊኖሯቸው ለሚችሉ ስጋቶች ምላሽ መስጠት | ለተሳታፊዎች ሊከብዱ የሚችሉ የህክምና እና ሌሎች ሙያዊ ቃላቶችን አለመጠቀም |
| ከተሳታፊዎች የሚነሱ ጥያቄዎች ግልፅ ካልሆኑ ማብራሪያ መጠየቅ | በምንም ምክንያት ሰዎች እንደዚህ ሊሆኑ ይችላሉ ብሎ አለመገመት፡ ለምሳሌ፡ አንድ ተሳታፊ ወንድ ስለሆነ ብቻ አያለቅስም ብሎ አለማሰብ |
| ተሳታፊዎችን በክብር እና በትህትና ማስተናገድ | ማንኛውንም ተሳታፊ በምንም ዓይነት ሁኔታ አለማንቋሸሽ ወይም አለመናቅ፤ ሌሎች ተሳታፊዎችም እንዲህ እንዲያደርጉ አለመፍቀድ |
| ተሳታፊዎች ሃሳባቸውን ለመሰብሰብ እና ለውይይቱ አስተዋፆ እንዲያደርጉ በቂ ጊዜ እና ቦታ መስጠት | በውይይቱ ደፈር ያሉ ተሳታፊዎች ብቻ እንዲናገሩና የሌሎች ተሳታፊዎች ሃሳብ እንዲዋጥ አለመፍቀድ |
| በውይይቱ የተነሱ ዋና ዋና ነጥቦችን አጠቃልሎ በውይይቱ መጨረሻ ማቅረብ | የተለዩ ሃሳቦችን ወይም መከራከሪያ ነጥቦችን አለመገደብ ሃሳቦችን ተሳታፊዎች እንዲቀበሉ አለማስገደድ |
| በውይይቱ ወቅት የተነሱ የተሳሳቱ አመለካከቶችን ማረም | ከራስ አስተሳሰብ ጋር የሚቀራረቡ ሰዎችን ማበረታታት እና የሚለዩትን አለማበረታታት |
| ተሳታፊዎች ያደመጡትን ጉዳይ እንዲያብላሉ ዝምታን በአግባቡ መጠቀም | |
| ለቡድኑ የገቡትን ቃል መጠበቅ፡ ለምሳሌ፣ የውይይቱን መጀመሪያ እና ማብቂያ ጊዜ፣ ላልተመለሱ ጥያቄዎች መልስ አፈላልጎ ማምጣት፣ ወዘተ | |

# የዚህ መመሪያ አጠቃቀም

ይህ መመሪያ የተዘጋጀው ውይይቱን ለሚመሩ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ወይም ሌሎች የእርካብ ራዲዮ ድራማ የአድማጮች ቡድን ለሚያቋቁሙ እና ውይይት ለሚመሩ ሰዎች ነው፡፡ አወያዮች የአድማጮች ቡድን ከማቋቋማቸው በፊት ይህን መመሪያ ማንበብ ይኖርባቸዋል፡፡ የአድማጭ ቡድኖች ተቋቁመው የአንድ ክፍል ውይይት ከማካሄዳቸው በፊት ዝግጅት ስለማድረግ የሚገልጸውን ክፍል ማንበብ ይኖርባቸዋል፡፡

ከዚህ መመሪያ ጋር ከተከታታይ ድራማው ውስጥ ተፈላጊዎቹን ክፍሎች የያዘው ሲዲ ወይም የፍላሽ ዲስክ አብሮ ቀርቧል፡፡ ይህ የውይይት መመሪያ እትም ከ 1 እስከ 12 ላሉት የድራማው ክፍሎች የተዘጋጀ ነው፡፡ የአድማጮች ቡድን በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ አንዷኛውን ክፍል ብቻ ማዳመጥ ይኖርባቸዋል፤ ከዚያ በመቀጠል በዚህ መመሪያ መሠረት ተያያዥ ውይይት ያደርጋሉ፡፡ ከ 13 እስከ 24 ላሉት የድራማው ክፍሎች ሌላ ራሱን የቻለ መመሪያ ይኖራል፡፡

# የአድማጮች ቡድን ማቋቋም

**1ኛ-** የአድማጮች ቡድን አባላት ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎችን ይለዩ፤ ከዚያም በሚቀርበው ክፍል ላይ እንዲገኙ ይጋብዟቸው። እርካብ የራዲዮ ድራማ የተዘጋጀው በቅርቡ ለተጋቡ ባልና ሚስት፣ ለእርጉዝ ሴቶችና ለባሎቻቸው እንዲሁም ከ2 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ላሏቸው ሴቶችና ወንዶች ነው። በመሆኑም የአድማጮች ቡድኖች እንዲህ ያሉ ሰዎችን ያካተቱ መሆን ይኖርባቸዋል። ቡድኑ ይበልጥ ፍሬያማ እንዲሆን አባላቱ ተመሳሳይ ፆታ ሊኖራቸው ይገባል። የቡድኑ አባላት እርስ በርስ በጣም የሚተዋወቁ ባይሆኑም ይመረጣል። ውይይቱ ይበልጥ የተሳካ እንዲሆን አንድ ቡድን ከ8 እስከ 12 አባላት ቢኖሩት ጥሩ ነው።

**2ኛ-** የቡድን ውይይቱ የሚካሄድበትን ቦታ ይምረጡ። ቦታው በቡድኑ እንዲካተቱ የመረጧቸውን ሰዎች በሙሉ ሊይዝ የሚችል ስፋት ሊኖረው ይገባል። ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ ለ2 ሰዓታት ወይም ከዚያ ለሚበልጥ ጊዜ በቦታው መጠቀም ትችሉ እንደሆነ ማጣራት ይኖርብዎታል። ተሳታፊዎቹ ዝናብ እና ፀሐይ እንዳይመታቸው ጥላ ያለበት ቦታ ቢሆን ይመረጣል።

**3ኛ-** የቡድን ውይይቱን በመምራት ረገድ ሊረዳዎት የሚችል አንድ ሰው ያዘጋጁ። ይህ ሰው የአድማጭ ቡድኑ በሚሰበሰብበት ጊዜ ሁሉ ተሳታፊዎች ዘና እንዲሉ የሚያደርጉ ዝግጅቶችን ያደርጋል፣ ማስታወሻ በመፃፍ ሊያግዝዎት ይችላል፣ እንዲሁም ውይይቱ ዘና ባለ መልኩ መጀመሩንና እንደ አስፈላጊነቱ ከአቅርቦት ጋር የተያያዙ ሌሎች ነገሮች መሟላታቸውን ይከታተላል።

**4ኛ-** እያንዳንዱ አባል ራሱን እንዲያስተዋውቅ እድል ይስጡ። ቡድኑ የተገናኘበት ዓላማ ምን እንደሆነ ይግለጹ እንዲሁም ሁሉም አባላት በቡድኑ ውስጥ ለመሳተፍ ፈቃደኛ መሆናቸውን ይጠይቁ። አንዱን የድራማ ክፍል አዳምጦ በዚያ ላይ መወያየት አንድ ሰዓት ከግማሽ ያህል ሊፈጅ እንደሚችል ለቡድኑ ያሳውቁ።

**5ኛ-** አባላቱ በቡድኑ ውስጥ ለመሳተፍ ፈቃደኝነታቸውን ከገለጹ በኋላ ቡድኑ የሚመራባቸውን ደንቦች በጋራ አውጡ። ቡድኑ በየስንት ጊዜ መሰብሰብ እንደሚኖርበት በደንቡ ውስጥ መጠቀስ ይኖርበታል። የስብሰባው ቀንና ሰዓት እንዲሁም ሌሎች ግልጽ ደንቦች መካተታቸው ቡድኑ በተሻለ ሁኔታ እንዲንቀሳቀስ ያስችላል።

**6ኛ-** ቀጥሎ በቀረበው መመሪያ መሠረት የመጀመሪያውን ክፍል ፕሮግራም አካሂዱ። ፕሮግራሙ ከመጀመሩ በፊት የሚደረጉ ዝግጅቶች
በየሳምንቱ የአድማጮች ቡድን ውይይቶችን ከማካሄዳችሁ በፊት ዝግጅት ማድረግዎት ወሳኝ ነገር ነው። የሚከተሉት ነጥቦች ዝግጅት ለማድረግ ይጠቅሙዎታል።

- ውይይቱ ከመደረጉ በፊት የሚቀርበውን የድራማውን ክፍል ያዳምጡ፤ ከክፍሉ ጋር ተዛማጅ የሆነውን የውይይት መመሪያም ያንብቡ። እንዲህ ማድረግዎት ከርዕሰ ጉዳዩና ውይይት ከሚካሄድባቸው ጥያቄዎች ጋር እንዲተዋወቁ ይረዳዎታል።
- የሳምንቱን ርዕሰ ጉዳይ በተመለከተ ጥያቄዎች ካሉዎት ውይይቱ ከመጀመሩ በፊት ስለ ጉዳዩ የሚያውቁ ሰዎችን (የጤና ሠራተኞች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ) ያነጋግሩ።
- በውይይቱ ላይ የተነሱ ቁልፍ ነጥቦችን በአጭሩ ለማስፈርና መልስ ያልተሰጠባቸውን ጥያቄዎች ለመጻፍ እስክሪብቶና ወረቀት መያዝ አይዘንጉ።
- ውይይቱን መምራት ከመጀመርዎት በፊት ተሳታፊዎች ዘና እንዲሉ ለማድረግ ወይም ውይይቱን ለመምራት የሚያስፈልጉት ነገሮች በሙሉ መሟላታቸውን ያረጋግጡ።
- ድራማውን ለማጫወት ያዘጋጁት ማጫወቻ የሚሠራ መሆኑንና ድምፁ ለተሳታፊዎች በሙሉ የሚሰማ መሆኑን ያጣሩ።

# የውይይቱ መመሪያዎች የሚተገበሩበት አጠቃላይ አካሄድ

1. <u>ሰላምታ/መግቢያ (5 ደቂቃ)</u>

ለተሳታፊዎች ሰላምታ ማቅረብ፤ በስብሰባው ላይ የተገኙ አዳዲስ አባላት ካሉ ለቡድኑ ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ መጋበዝ

2. <u>ያለፈው ሳምንት ክለሳ (5 ደቂቃ)</u>

ባለፈው ሳምንት ከቀረበው ከተከታታዩ የድራማ ክፍል ምን እንደሚያስታውሱ ተሳታፊዎችን መጠየቅ፤ በውይይቱ ላይ ተነስተው የነበሩ ቁልፍ ነጥቦችን መከለስ

3. <u>ከዕለቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር የተያያዙ አድማጮችን የሚያዝናኑ ዝግጅቶች</u>

እያንዳንዱ ክፍል ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ዝምድና ያለው አድማጮችን ዘና የሚያደርግ ማነቃቂያ ጨዋታ አለው። ይህም ተሳታፊዎች ዘና እንዲሉ፣ ትንሽ እንዲንቀሳቀሱና እንዲነቃቁ ያስችላል።

4. <u>ድራማውን ማጫወት (12 – 15 ደቂቃ)</u>

ለሳምንቱ የተዘጋጀውን የድራማ ክፍል ማጫወት (የእያንዳንዱ ተውኔት ፍሬ ሐሳብ በዚህ የውይይት መምሪያ የተካተተ ሲሆን ይህም ለእርስዎ ብቻ የተዘጋጀ ማመሳከሪያ ነው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለተሳታፊዎች አያንብቡ።)

**5. <u>ውይይቱን መምራት (30-40 ደቂቃ)</u>**

ለተውኔቱ የተዘጋጁት የማወያያ ጥያቄዎች በዚህ መመሪያ ላይ ቀርበዋል። ውይይቱን በተሳካ ሁኔታ ለማካሄድ እያንዳንዱን ጥያቄ በቅደም ተከተሉ መሠረት መጠየቅ፤ ተሳታፊዎች ሐሳብ ለመስጠት እኩል አጋጣሚ እንዲያገኙ ጥረት ማድረግ፤ በተቻለ መጠን ውይይቱ ከርዕሰ ጉዳዩ እንዳይወጣ መጠንቀቅ እና ማስታወሻ መያዝ

**6. <u>ቁልፍ ነጥቦችን በአጭሩ ማቅረብ (10-15 ደቂቃ)</u>**

በውይይቱ ላይ የተነሱትን ቁልፍ ነጥቦች ጨምቆ ማቅረብ (በክለሳው ላይ መጠቀስ ያለባቸው ጉዳዮች እንዳይረሱ የክለሳ ነጥቦቹ በዚህ መመሪያ ላይ ቀርበዋል)

**7. <u>የቤት ሥራ መስጠት (5 ደቂቃ)</u>**

ቡድኑ ከተበተነ በኋላ ተሳታፊዎች ሊያደርጓቸው የሚችሉ አንዳንድ ቀለል ያሉ ሥራዎችን መስጠት (ለተሳታፊዎቹ ሊሰጡ የሚችሉ ቀለል ያሉ ተግባሮች በዚህ መመሪያ ላይ ቀርበዋል።

# በእርካብ የራዲዮ ድራማ ላይ የሚደረግ ውይይት መመሪያዎች

## ክፍል 1
# በጫና የሚፈፀም ጋብቻ

ይህ የውይይት ክፍል የመጀመሪያው በመሆኑ ከሌሎቹ ክፍሎች በተወሰነ መጠን ለየት ይላል፡፡

**<u>ውይይቱ የሚወስደው የጊዜ ርዝመት በግምት</u>**

1 ሰዓት ከ25 ደቂቃ

**<u>የውይይቱ ዓላማ</u>**

ሰዎች ወደ ትዳር ዓለም የሚገቡባቸውን ምክንያቶች እና ለማግባት ውሳኔ ላይ መድረስ ያለበት እንዴት እንደሆነ ለመመርመር

**<u>የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች</u>**

ራዲዮ ድራማውን ለማጫወት የሚያስችል ማጫወቻ፣ ለውይይቱ የተዘጋጀው የራዲዮ ድራማ ክፍል በፍላሽ ዲስክ ወይም በሲዲ፣ እስክርቢቶ፣ ማስታወሻ መያዣ ወረቀት፣ ፍሊፕቻርት፣ ማርከሮች

**1ኛ፦ ሰላምታ ማቅረብ (5 ደቂቃ)**

መጀመሪያ ለተሳታፊዎቹ መልካም አቀባበል ያድርጉ፡፡ ቡድኑ የተቋቋመበት ዓላማ ምን እንደሆነ ይግለጹ፤ ተሳታፊዎች የቡድኑ አባል ለመሆን ላሳዩት ፈቃደኝነትም ያመስግኗቸው፡፡ ተከታታይ የሆነ አዝናኝ ድራማ አብራችሁ ካዳመጣችሁ በኋላ ምን እንደተሰማችሁ እና ምን እንደተገነዘባችሁ እንደምትወያዩ ያብራሩ፤ እንዲሁም አብዛኞቹ ክፍሎች ከአንድ ሰዓት እስከ አንድ ሰዓት ተኩል የሚደርስ ጊዜ እንደሚወስዱ ያሳውቁ፡፡ እስከ 2 ሰዓት የሚፈጁት ክፍሎች ጥቂት መሆናቸውን ያስታውሷቸው፡፡

**2ኛ፦ መግቢያ እና ትውውቅ (12 ደቂቃ)**

አድማጮች ስማቸውን፣ ሥራቸውንና የት እንደሚኖሩ በመናገር ማንነታቸውን ለቡድኑ እንዲያስተዋውቁ አጋጣሚ ስጡ፡፡ ፈቃደኛ ከሆኑ ከቤተሰብ ሕይወታቸው ወይም ከሚኖሩበት ማኅበረሰብ ጋር በተያያዘ የሚያሳስባቸውን አንድ ነገር እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፡፡

**3ኛ፦ ቡድኑ የሚመራባቸውን ደንቦች ማውጣት (10 ደቂቃ)**

ክፍለ ጊዜያቱ አስደሳች እና ፍሬያማ እንዲሆኑ አንዳንድ ደንቦችን በጋራ ማውጣት አስፈላጊ መሆኑን ለቡድኑ አባላት ይናገሩ፡፡ ምን ዓይነት ደንቦች መውጣት እንደሚኖርባቸው ይጠይቁ፤ ከዚያም የሚሰጡትን መልስ በፍሊፕ ቻርት ላይ በማርከር ይጻፏቸው፡፡ የሚከተሉት ነጥቦች በደንቦቹ ላይ መካተታቸውን ያረጋግጡ፡፡

- የሌሎችን አመለካከት ማክበር
- በንቃት መከታተል
- ሰዓት ማክበር

ደንቦቹን የጻፉበትን ወረቀት ሁሉም አባላት ማየት እንዲችሉ ግድግዳ ላይ ይለጥፉት፡፡ ወረቀቱን ግርግዳው ላይ ይተዉት ወይም ቡድኑ በተሰበሰበ ቁጥር ይለጥፉት፡፡

በተጨማሪም የቡድኑ አባላት በየስንት ጊዜው መሰብሰብ እንደሚፈልጉ ይጠይቋቸው፤ እንዲሁም የምትገናኙበትን ቀንና ሰዓት በጋራ ወስኑ፡፡ ቡድኑ በየሳምንቱ ቢገናኝ ይመረጣል፡፡

**4ኛ፦ የድራማው የመጀመሪያውን ክፍል ማጫወት (15 ደቂቃ)**

**ከድራማው ተቀንጭቦ የተወሰደ፦**

ንጹሕ ሳትወድ በግዷ ተስፋን ልታገባ ነው፤ ተስፋ ወደ ቤተሰቦቿ ሽማግሌዎች በመላክ ጋብቻውን እንዲፈቅዱ ጥያቄ አቀርቧል፡፡ ንጹሕ በጋብቻው ደስተኛ አይደለችም፤ ምክንያቱም ጎረቤቷና የትምህርት ቤት ጓደኛዋ የሆነውን ብርሃኑን ትወድደዋለች፡፡ በተጨማሪም የመማር እንጂ የማግባት ፍላጎት የላትም፡፡ ሆኖም ሞት አፋፍ ላይ ያሉትን አባቷ ፍላጎት ለማሳካት ስትል ተስፋን ለማግባት ተስማማች፡፡ ተስፋ ደግሞ እቅዱ ስለሰመረለት የልብ ልብ ተሰምቶታል፡፡

የሠርጉ ዕለት ሙሽራውና ሚዜዎቹ በማለፊያ ቀበሌ የሚገኙትን ሁለቱን መንደሮች የሚያገናኘውን ድልድይ እየተሻገሩ ሳለ ድልድዩ ፈረሰ፡፡ ተስፋ ጉዳት ቢደርስበትም የሠርጉ ሥነ ሥርዓት ተከናወነ፡፡ ተስፋ ሙሽሪትን ወሰደ፤ የንጹሕ አባት አቶ ካሳም ኃይላቸውን እንደምንም አሰባስበው ሙሽሮቹን መረቋቸው፡፡

**5ኛ፦ ውይይቱን መምራት (30 ደቂቃ)**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንድ በአንድ በመጠየቅ ውይይቱን ይምሩ፡፡ ውይይቱን በተመደበው ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ እንድትችሉ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከሚያስፈልገው ጊዜ በላይ አትውሰዱ፡፡

1. ንጹሕ ተስፋን ለማግባት የወሰነችው ለምንድን ነው?
2. በጋብቻው አልስማማም ያላለችው ለምንድን ነው?
3. እናንተ ባላችሁበት ማኅበረሰብ ውስጥ ሰዎች ትዳር የሚመሠርቱት ለምንድን ነው?
4. ሰዎች ማግባት የሚኖርባቸው መቼ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?
5. ሰዎች ትዳር ሲመሰርቱ ዋናው ውሳኔ ሰጪ መሆን ያለበት ማን ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?

**6ኛ- ዋና ዋና ሃሳቦችን በአጭሩ ማቅረብ (10 ደቂቃ)**

በውይይቱ ላይ የተነሱትን ቁልፍ ሃሳቦች ጨምቀው ያቅርቡ፡፡ ከዚህ በታች የተገለፁትን ነጥቦች በክለሳው ወቅት ማንሳትዎትን አይዘንጉ፡፡

- ሰዎች ጋብቻ የሚመሠርቱት በፍላጎታቸው ሊሆን ይገባዋል፡፡
- በብዙ ማኅበረሰቦች ውስጥ ሴቶች የሚዳሩት ፈቃደኝነታቸው ሳይጠየቅ ነው፤ እንዲህ መደረጉ ትክክል አይደለም፡፡
- ከዚህም ሌላ ሴቶች ትዳር ሲመሰርቱ ዕድሜያቸው 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ መሆን አለባቸው፡፡ ይህም መውለድ በምትችልበት ዕድሜ ላይ እንድትገኝ የሚያስችላት ከመሆኑም ሌላ የራሷን ውሳኔ ለማድረግ የሚያስችል የማመዛዘን ችሎታ ይኖራታል፡፡ ከ18 ዓመት በታች የሆናቸው ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ማግባት እንደማይችሉ የኢትዮጵያ ሕግ ይደነግጋል፡፡
- ሰዎች ወደ ትዳር ዓለም ሲገቡ በገንዘብም ሆነ በሥነ ልቦና ዝግጁ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ለማግባት የመጨረሻውን ውሳኔ ማድረግ የሚኖርባቸው ሙሽሪትና ሙሽራው ናቸው፤ በዚህ ረገድ ማንም ሊወስንላቸው አይገባም፡፡ በተለይ ደግሞ ሴቶች ጋብቻ ለመመሥረት መስማማታቸው የግድ አስፈላጊ ነው፡፡

**7ኛ- ቀላል የቤት ሥራ (3 ደቂቃ)**

አድማጮች እንድታገባ ጫና የሚደረግባት ሴት ልጅ ወይም ከ18 ዓመት በታች የሆነች ልጅ ብታጋጥማቸው ምን እንደሚያደርጉ እንዲያስቡ ሃሳባቸውንም በጽሑፍ እንዲያሰፍሩ ይጠይቁ፡፡ እዚያው ባሉበት መልስ እንዲሰጡ አይጠበቅባቸውም፤ ከዚህ ይልቅ ወደ ቤት ከሄዱ በኋላ በሳምንቱ ውስጥ የሚያከናውኑት ሥራ ነው፡፡

**8ኛ- ለአድማጮች ምስጋና ካቀረቡ በኋላ ስብሰባው ማብቃቱን ያሳውቁ**

## ክፍል 2

# አዳዲስ ጅምሮች

**ክፍሉ የሚወስደው የጊዜ ርዝመት በግምት**

1 ሰዓት

**የክፍሉ ዓላማ**

አድማጮች በሕይወታቸው ወደ አዲስ ምዕራፍ (ጋብቻ፣ ልጅ መውለድ፣ ጓደኛነት መመሥረት፣ ወዘተ) ለመግባት ሲወስኑ በዚ ዝግጅት እንዲያደርጉ ለመርዳት

**የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች**

ራዲዮ ድራማውን ለማጫወት የሚያስችል ማጫወቻ፣ ለቀኑ የተዘጋጀው የራዲዮ ድራማ ክፍል በፍላሽ ዲስክ ወይም በሲዲ፣ እስክርቢቶ፣ ማስታወሻ መያዣ ወረቀት

**1ኛ- ሰላምታ ማቅረብ (2 ደቂቃ)**

**2ኛ- ያለፈው ሳምንት ክለሳ (5 ደቂቃ)**

አድማጮች ባለፈው ሳምንት ከቀረበው የድራማ ክፍል ምን እንደሚያስታውሱ ይጠይቁ። ተሳታፊዎቹ ከንጹሕና ከተስፋ ታሪክ እንዲሁም ከድልድዩ ጋር በተያያዘ ከተከሰተው ሁኔታ የሚያስታውሱትን ነገር እንዲናገሩ ይጠይቋቸው።

ባለፈው ሳምንት የተሰጣቸውን ትንሽ የቤት ሥራ ሠርተው እንደሆነ ይጠይቋቸው።

**3ኛ- ዘና የሚያደርጉ ዝግጅቶች (5 ደቂቃ)**

ተሳታፊዎች በህይወታቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ስላደረጉት አንድ ነገር ለቡድኑ እንዲያካፍሉ ይጠይቋቸው። ጊዜ እስከበቃ ድረስ ፈቃደኛ ለሆኑ ተሳታፊዎች ተሞክሯቸውን እንዲያካፍሉ ዕድል ይስጡ። በተቻለ መጠን ከአምስት ደቂቃ አይውሰዱ።

**4ኛ- ሁለተኛውን ክፍል ድራማ ማጫወት (15 ደቂቃ)**

**ከድራማው ተቀንጭቦ የተወሰደ**

ተስፋ በዚያው በተጋቡበት ዕለት ምሽት የፆታ ግንኙነት መፈጸም አለብን ይላል፤ ንጹሕ ብታቅማማም ፍላጎቱን ይፈፅማል። በዚያው ሌሊት የንጹሕ አባት ሕይወታቸው ያልፋል። በማግስቱ ጠዋት ንጹሕ አባቷን ለማየት የግድ ወደ ቤት መሄድ እንደምትፈልግ ትናገራለች፤ ነገር ግን በሠርግ ማግስት ሚስት ባሏን ጥላ መሄዷ ፍጹም በባሕሉ እንደማይፈቀድ ነግሮ ከለከላት። ባልና ሚስቱ ብዙም ሳይቆይ መርዶው ይነገራቸዋል።

ጠዋት ላይ ጎረቤቶች ድልድዩ ስለፈረሰ አስከሬኑን እንዴት ወደ መቃብር ቦታው አሻግረው መውሰድ እንደሚችሉ ይወያያሉ። ምንም ምርጫ ስለሌላቸው በረጅሙና በአስቸጋሪው መንገድ ለመሄድ ይወስናሉ። ይሁንና ሦስት ሰዎች እነሱን ወክለው የቀበሌ አስተዳደሩን እንዲያናግሩላቸው ይመርጣሉ።

ንጹሕ አባቷ ከመሞታቸው በፊት ቤት ሄዳ ማየት እንዳትችል ተስፋ ስለከለከላት ተቆጥታለች። ተስፋ ምግብ እንድትበላ ሲጠይቃት እምቢ ትላለች፤ ይሁንና ለብርሃኑ የውስጧን አውጥታ ትነግረዋለች። ይህ ደግሞ ተስፋን ያበሳጨዋል።

**5ኛ፦ ውይይቱን መምራት (25 ደቂቃ)**

ንጹሕ ከተስፋ ጋር አዲስ ሕይወት በጀመረችበት እለት አባቷ መሞታቸውንና ሕይወቷ በአንድ ጀንበር ሙሉ በሙሉ እንደተቀየረ አድማጮችን ያስታውሷቸው። የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንድ በአንድ በመጠየቅ ውይይቱን ይምሩ። ውይይቱን በተመደበው ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ እንድትችሉ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከሚያስፈልገው በላይ ጊዜ አትውሰዱ።

1. በዚህ ጊዜ ንጹሕን የሚያሳስባት ነገር ምን ይመስላችኋል?
2. ንጹሕ ከተስፋ ጋር የመሠረተችው ትዳር ጥሩ እንዲሆን ምን ማድረግ ይኖርባታል?
3. ሰዎች ወደ አዲስ ነገር ሲገቡ በቂ ዝግጅት ባያደርጉ ምን ያጋጥማቸዋል ትላላችሁ? በዚህ ጉዳይ የራሳችሁ ወይም የምታውቁት ሰው ተሞክሮ ካለ እስቲ አካፍሉን
4. ሰዎች በሕይወታቸው ውስጥ አዲስ ነገር እንዲጀምሩ የሚያነሳሳቸው ምንድን ነው?
5. ሰዎች በሕይወታቸው ውስጥ አዲስ ነገር ሲጀምሩ ምን ዓይነት ዝግጅቶች ማድረግ ይኖርባቸዋል?

**6ኛ፦ ዋና ዋና ሃሳቦችን በአጭሩ ማቅረብ (5 ደቂቃ)**

በውይይቱ ላይ የተነሱትን ቁልፍ ሃሳቦች ጨምቀው ያቅርቡ። ከዚህ በታች የተገለፁትን ነጥቦች በክለሳው ወቅት ማንሳትዎትን አይዘንጉ።

- ሰዎች በሕይወታቸው ውስጥ አዲስ ነገሮችን ይጀምራሉ። ሰዎች በሕወታቸው ውስጥ አዲስ ነገር ሲጀምሩ መጨናነቃቸው ያለ ነገር ነው። እንደ ጋብቻና ልጅ መውለድ ያሉ አዳዲስ ጅምሮች መጨረሻቸው ስለማይታወቅ አስፈሪ ሊሆኑ ይችላሉ።
- በሕይወት ውስጥ አዳዲስ ነገሮች የሚጀመሩት ወይ ታስቦባቸው አሊያም ደግሞ በአጋጣሚ ይሆናል። ፈተና ቢያጋጥማቸሁም በቀላሉ ለማለፍ ትችላላችሁ። ለሚያጋጥሟችሁ ለውጦች ጥሩ እቅድ ካወጣችሁ ሕይወታችሁ ይበልጥ ትርጉም ያለው ይሆናል። በቅርቡ የምታደርጉትን ለውጥ አስቀድማችሁ ማወቅ ከቻላችሁ አስፈላጊዎቹን ዝግጅቶች ማድረግ ትችላላችሁ።

**7ኛ፦ ቀላል የቤት ሥራ (3 ደቂቃ)**

አድማጮች በህይወታቸው ምን አዲስ ነገር ሊጀምሩ እንዳሰቡ እና ምን ዓይነት ዝግጅቶች ሊያደርጉ እንደሚገባቸው እንዲያሰላስሉ እና በፅሑፍ እንዲያሠፍሩ ጠይቋቸው።

**8ኛ፦ ለአድማጮች ምስጋና ካቀረቡ በኋላ ስብሰባው ማብቃቱን ያሳውቁ**

## ክፍል 3

# በባል እና ሚስት መካከል የሚደረግ ግልፅ ውይይት

**<u>ክፍሉ የሚወስደው የጊዜ ርዝመት በግምት</u>**

1 ሰዓት ከ30 ደቂቃ

**<u>የክፍሉ ዓላማ</u>**

የቤተሰብ ምጣኔን በተመለከተ በባልና ሚስት መካከል ግልጽ ውይይት እንዲኖር ለማበረታታት

**<u>የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች</u>**

ራዲዮ ድራማውን ለማጫወት የሚያስችል ማጫወቻ፣ ለቀኑ የተዘጋጀው የራዲዮ ድራማ ክፍል በፍላሽ ዲስክ ወይም በሲዲ፣ እስክርቢቶ፣ ማስታወሻ መያዣ ወረቀት

**1ኛ- ሰላምታ ማቅረብ (2 ደቂቃ)**

**2ኛ- ያለፈው ሳምንት ክለሳ (5 ደቂቃ)**

አድማጮች ባለፈው ሳምንት ከቀረበው ተውኔት ምን እንደሚያስታውሱ ይጠይቁ፡፡ ተሳታፊዎቹ ከንጹሕና ከተስፋ ታሪክ እንዲሁም ከድልድዩ ግንባታ ጋር በተያያዘ ከተከሰተው ሁኔታ የሚያስታውሱትን ነገር እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፡፡

ባለፈው ሳምንት የተሰጣቸውን የቤት ሥራ ሠርተው እንደሆነ ይጠይቋቸው፡፡

**3ኛ- ዘና የሚያደርጉ ዝግጅቶች (5 ደቂቃ)**

ተሳታፊዎች ባለቤታቸውን ማን ብለው እንደሚጠሩ (የቅፅል ስም አውጥተውላቸው ከሆነ) ይጠይቋቸው፡፡ ካልሆነ ምን ዓይነት ቅፅል ስም ቢያወጡላቸው እንደሚወድዱ ይጠይቋቸው፡፡ ይህንን ስም ለምን እንደመረጡላቸውም ይጠይቋቸው፡፡ በተቻለ መጠን ከአምስት ደቂቃ በላይ አይውሰዱ፡፡

**4ኛ- ሦስተኛውን ክፍል ድራማ ማጫወት (15 ደቂቃ)**

**ከድራማው ተቀንጭቦ የተወሰደ**

ንጹሕ ለአባቷ ሞት ሐዘን ተቀምጣ ከጨረሰች በኋላ ከባሏና ከአማቾቿዋ ጋር ሆና ወደ አዲሱ ቤቷ ተመልሳለች፡፡ በቅርቡ ልጅ የመውለድ ፍላጎት እንደሌላት በመናገሯ ከአማቷ ከወ/ሮ ጌጤ ጋር ቅራኔ ውስጥ ገብታለች፡፡ በዚህ ጊዜ ተስፋ ለንጹሕ ጥብቅና ይቆማል፤ ይሁንና ከሁለት የቅርብ ጓደኞቹ መካከል አንዱ የሆነው ደርቤ በቀልድ መልክ ብርሃኑ በሚስቱ ላይ ዓይኑን ሊጥልባት እንደሚችል ከነገረው በኋላ ተጨንቋል፡፡

የቀበሌው አስተዳደር ቀበሌው ድልድዩን ለመገንባት እንዲረዳቸው ለመጠየቅ ሕዝቡ የወከላቸውን አቶ አማንን፣ አቶ አያሌውንና ወ/ሮ በለጤን በዚህ ዓመት ለግንባታው የሚሆን ባጀት እንደሌለ ያሳውቃቸዋል፡፡ ተወካዮቹ አንድ አማራጭ ይዘው ወደ ሳብረተሰቡ የተመለሱ ሲሆን ይህም ድልድዩን ለመገንባት የአካባቢው ነዋሪ ገንዘብ ያዋጣ የሚል ነው፡፡

**5ኛ፦ ውይይቱን መምራት (45 ደቂቃ)**

በመጨረሻው ትዕይንት ላይ በንጹሕና በወ/ሮ ጌጤ መካከል ተፈጥሮ በነበረው ውጥረት ላይ ተመሥርተው ውይይቱን ያስቀጥሉ፡፡ ተስፉ የሰጠው ምላሽ እናትየውን አሳዝኗቸው እንደነበር ተሳታፊዎቹን ያስታውሷቸው፡፡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንድ በአንድ በመጠየቅ ውይይቱን ይምሩ፡፡ ውይይቱን በተመደበው ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ እንድትችሉ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከሚያስፈልገው በላይ ጊዜ አትውሰዱ፡፡

1. ንጹሕ ልጅ መውለድ አልፈልግም የሚል አቋም የያዘችው ለምንድን ነው?
2. ንጹሕ ማርገዝ እንደማትፈልግ በተናገረች ጊዜ ወ/ሮ ጌጤ ሲቆጡ ተስፉ ምን ምላሽ መስጠት ነበረበት?
3. እናንተ በምትኖሩበት አካባቢ ብዙ ሰዎች ልጅ መቼ መውለድ እንዳለባቸው የሚወስኑት እንዴት ነው?
4. ልጅ ለመውለድ በሚደረገው ውሳኔ በአብዛኛው የእነማን ተሳትፎ አለበት?
5. በአካባቢያችሁ ከእርግዝናና ልጅ ከመውለድ ጋር በተያያዘ አብዛኞቹ ባሎች ለሚስቶቻቸው ድጋፍ የሚሰጡት እንዴት ነው?
6. አንዲት ሴት ማርገዝ ይኑርባት አይኑርባት መወሰን ያለበት ማን ነው?
7. ልጅ ለመውለድ ወይም ላለመውለድ ውሳኔ መደረግ ያለበት እንዴት ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?
8. ውሳኔ ከማድረግ ጋር በተያያዘ የባሎች ሚና ምን መሆን አለበት?
9. ልጅ መውለድን በተመለከተ ሚስቶች ከባሎቻቸው ጋር ለመወያየት ምን ማድረግ አለባቸው? ባሎችስ ምን ማድረግ አለባቸው?

**6ኛ፦ ዋና ዋና ሃሳቦችን በአጭሩ ማቅረብ (15 ደቂቃ)**

በውይይቱ ላይ የተነሱትን ቁልፍ ሃሳቦች ጨምቀው ያቅርቡ። ከዚህ በታች የተገለፁትን ነጥቦች በክለሳው ወቅት በሚገባ ማንሳትዎትን አይዘንጉ።

- መቼ ብንወልድ ይሻላል የሚለውን ውሳኔ ማድረግ የሚኖርባቸው ባልና ሚስት ናቸው። ሌሎች ሰዎች የሚሰጧቸውን ምክር መስማት ቢኖርባቸውም እንኳ ምንጊዜም ቢሆን የመጨረሻውን ውሳኔ ማድረግ ያለባቸው እነሱ ናቸው።
- ባልና ሚስቱ ልጅ እንውለድ ወይስ አንውለድ የሚለውን ሲወስኑ የገንዘብ አቅማቸውን፣ ማኅበራዊ ሕይወታቸውን፣ በስሜታቸው ላይ የሚፈጥርባቸውን ጫና እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮችን ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል። ሁለቱ ያሉበትን ሁኔታ በትክክል የሚያውቁት ራሳቸው ናቸው። ልጆቻቸውን በጥሩ ጤንነትና ሥነ ምግባር ማሳደግ የእነሱ ኃላፊነት ነው። ስለዚህ መቼ እንውለድና ስንት ልጆች እንውለድ የሚለውን የመጨረሻ ውሳኔ ማድረግ የሚኖርባቸው ሁለቱ ናቸው።
- ባልና ሚስቶች መቼ እንውለድ በሚለው ጉዳይ ሲወያዩ እርስ በእርስ መደማመጥና የትዳር ጓደኛቸውን ስሜት ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው። ልጅ ማሳደግ ትልቅ ኃላፊነት ስለሆነ ልጁን በጥሩ ጤንነትና ሥነ ምግባር አንጾ ለማሳደግ ሁለቱ እርስ በርስ መደጋገፍ ይኖርባቸዋል። በመሆኑም ልጅ ለመውለድ የሚወስኑት ሁለቱም አምነውበት እና ተስማምተው መሆን ይኖርበታል።

**7ኛ፦ ቀላል የቤት ሥራ (3 ደቂቃ)**

ተሳታፊዎች መቼ ልጅ ለመውለድ እንደሚፈልጉ እንዲያስቡ እና በዚህ ጉዳይ ላይ ቤት ሲሄዱ ከትዳር ጓደኛቸው ጋር እንዲወያዩ ይጠይቋቸው።

**8ኛ፦ ለአድማጮች ምስጋና ካቀረቡ በኋላ ስብሰባው ማብቃቱን ያሳውቁ**

## ክፍል 4

# ከቤተሰብ ዕቅድ ጋር በተያያዘ የወንዶች ተሳትፎ

**<u>ክፍሉ የሚወስደው የጊዜ ርዝመት በግምት</u>**

1 ሰዓት ከ10 ደቂቃ

**<u>የክፍሉ ዓላማ</u>**

ወንዶች ከቤተሰብ ምጣኔ ጋር በተያያዘ ተሳትፎ እንዲያደርጉ እና ድጋፍ እንዲሰጡ ለማበረታታት

**<u>የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች</u>**

ራዲዮ ድራማውን ለማጫወት የሚያስችል ማጫወቻ፣ ለቀኑ የተዘጋጀው የራዲዮ ድራማ ክፍል በፍላሽ ዲስክ ወይም በሲዲ፣ እስክርቢቶ፣ ማስታወሻ መያዣ ወረቀት

**1ኛ፦ ሰላምታ ማቅረብ (2 ደቂቃ)**

**2ኛ፦ ያለፈው ሳምንት ክለሳ (5 ደቂቃ)**

አድማጮች ባለፈው ሳምንት ከቀረበው ድራማ ምን እንደሚያስታውሱ ይጠይቁ። ተሳታፊዎቹ ከንጹሕና ከተስፋ ታሪክ እንዲሁም ከድልድዩ ግንባታ ጋር በተያያዘ ከተከሰተው ሁኔታ የሚያስታውሱትን ነገር እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው።

ባለፈው ሳምንት የተሰጣቸውን የቤት ሥራ ሠርተው እንደሆነ ይጠይቋቸው።

**3ኛ፦ ዘና የሚያደርጉ ዝግጅቶች (5 ደቂቃ)**

ወንዶች ማርገዝ እና መውለድ ቢኖርባቸው ኑሮ ምን ሊሰማቸው እንደሚችል ተሳታፊዎችን ይጠይቋቸው። ተሳታፊዎች የሚያቀርቧቸው ምላሾች የሚያስቁ እና የሚያወያዩ ሊሆኑ ይችላሉ። በተቻለ መጠን ከአምስት ደቂቃ በላይ አይውሰዱ።

**4ኛ፦ አራተኛውን ክፍል ድራማ ማጫወት (15 ደቂቃ)**

**ከድራማው ተቀንጭቦ የተወሰደ**

ንጹሕና ተስፋ ተደስተው እየኖሩ ያሉ ይመስላል። ይሁን እንጂ ብርሃኑና ሌሎቹ የንጹሕ ጓደኞች ሊጠይቋቸው ቤታቸው በመጡ ጊዜ ነገሮች መጥፎ መልክ ያዙ። የንጹሕ ጓደኛ ውልታ ንጹሕ አሁን ትዳር ስለመሠረተች ወሊድ መከላከያ መጠቀሟን ማቆም እንዳለባት ተስፋ ሳይሰማቸው ትነግራታለች። ንጹሕ ግን ትምህርቷን የመቀጠል ሐሳብ ስላላት በውልታ ሐሳብ አልተስማማችም። በሌላ በኩል ብርሃኑ ተስፋ 8ኛ ክፍልን ማለፍ ባለመቻሉ ያፌዝበታል። ተስፋም በጣም ይናደዳል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የአካባቢው ነዋሪዎች በጊዜያዊነት ድልድዩን ከእንጨት ለመሥራት ይስማሙና ሥራው ይጀመራል።

**5ኛ፦ ውይይቱን መምራት (30 ደቂቃ)**

ንጹሕና ውልታ ስለ ቤተሰብ ምጣኔ የተነጋገሩትን አስመልክቶ እንደምትወያዩ ለአድማጮች ንገራቸው፡፡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመጠቀም ውይይቱን ይምሩ፡፡ ውይይቱን በተመደበው ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ እንድትችሉ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተመደበው በላይ ጊዜ አትውሰዱ፡፡

1. ንጹሕ የወሊድ መቆጣጠሪያ እንደምትጠቀም ለተስፋ ያልነገረቸው ለምንድን ነው?
2. ተስፋ እሱ ሳያውቅ ሚስቱ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት እንደምትጠቀም ሲደርስበት ምን ምላሽ የሚሰጥ ይመስላችኋል?
3. በምትኖሩበት አካባቢ ብዙ ወንዶች ስለ ቤተሰብ እቅድ ያላቸው አመለካከት ምንድን ነው?
4. ወንዶች በቤተሰብ እቅድ ረገድ ምን ድርሻ ሊኖራቸው ይገባል ትላላችሁ?
5. ወንዶች የቤተሰብ እቅድን በተመለከተ ተሳትፎ ማድረግ የሚኖርባቸው ለምንድን ነው?

**6ኛ- ዋና ዋና ሃሳቦችን በአጭሩ ማቅረብ (10 ደቂቃ)**

በውይይቱ ላይ የተነሱትን ቁልፍ ሃሳቦች ጨምቀው ያቅርቡ፡፡ ከዚህ በታች የተገለፁትን ነጥቦች በክለሳው ወቅት ማንሳትዎትን አይዘንጉ፡፡

- የቤተሰብ እቅድ ሰዎች መውለድ የሚፈልጉትን የልጅ ቁጥር እንዲወስኑና በምርጫቸው መሠረት አራርቀው እንዲወልዱ ያስችላቸዋል፡፡
- የቤተሰብ እቅድ እናትየው ከወሊድ በኋላ ጤንነቷ እንዲመለስላት ያግዛል፣ ወላጆች ለልጆቻቸው በቂ ፍቅርና ትኩረት እንዲሰጡ ያስችላል፤ እንዲሁም ቤተሰብን በማስተዳደር ረገድ ያለባቸው ሸክምና ኃላፊነት እንዲቀልል ያደርጋል፡፡ በመሆኑም ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ለቤተሰብ እቅድ ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡
- ወንዶች ሚስቶቻቸው የቤተሰብ እቅድ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማበረታታት ይኖርባቸዋል፤ ምክንያቱም ይህ በሚስቶቻቸው ጤንነትም ሆነ በቤተሰባቸው ደኅንነት ላይ ለውጥ ያመጣል፡፡

**7ኛ- ቀላል የቤት ሥራ (3 ደቂቃ)**

ሴት ተሳታፊዎች የቤተሰብ እቅድ አገልግሎቶችን መጠቀም ቢፈልጉ ከባሎቻቸው ምን ዓይነት ድጋፍ ማግኘት እንደሚፈልጉ እንዲያስቡ እና ከባሎቻቸው ጋር እንዲወያዩ ይጠይቋቸው፡፡ ወንዶቹን ደግሞ ሚስቶቻቸው የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ምን ድጋፍ መስጠት እንደሚችሉ እንዲያስቡ እና ከሚስቶቻቸው ጋር እንዲወያዩ ይጠይቋቸው፡፡

**8ኛ- ለአድማጮች ምስጋና ካቀረቡ በኋላ ስብሰባው ማብቃቱን ያሳውቁ**

## ክፍል 5
# የጋራ ችግሮችን ለመፍታት የማህበረሰብ ተሳትፎ

**ክፍሉ የሚወስደው የጊዜ ርዝመት በግምት**

1 ሰዓት

**የክፍሉ ዓላማ**

ተሳታፊዎች የኅብረተሰቡን የጤና እክሎችን ነቅሰው እንዲያወጡና የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በማፈላለግ ላይ እንዲመክሩ ለማበረታታ

**የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች**

ራዲዮ ድራማውን ለማጫወት የሚያስችል ማጫወቻ፣ ለቀኑ የተዘጋጀው የራዲዮ ድራማ ክፍል በፍላሽ ዲስክ ወይም በሲዲ፣ እስክርቢቶ፣ ማስታወሻ መያዣ ወረቀት

**1ኛ- ሰላምታ ማቅረብ (2 ደቂቃ)**

**2ኛ- ያለፈው ሳምንት ክለሳ (5 ደቂቃ)**
አድማጮች ባለፈው ሳምንት ከቀረበው የራዲዮ ድራማ ምን እንደሚያስታውሱ ይጠይቁ። ተሳታፊዎቹ ከንጹሕና ከተስፋ ታሪክ እንዲሁም ከድልድዩ ግንባታ ጋር በተያያዘ ከተከሰተው ሁኔታ የሚያስታውሱትን ነገር እንዲናገሩ ይጠይቋቸው።

ባለፈው ሳምንት የተሰጣቸውን የቤት ሥራ ሠርተው እንደሆነ ይጠይቋቸው።

**3ኛ- ዘና የሚያደርጉ ዝግጅቶች (5 ደቂቃ)**
ፈቃደኛ የሆኑ ተሳታፊዎች የህብረት ስራ በሚሰራበት ጊዜ የሚዘፈን አንድ የሚያውቁትን ዘፈን እንዲጫወቱ ይጠይቋቸው። ከተቻለ አንዱ ተሳታፊ ሲዘፍኑ ሌሎቹ እንዲያጅቡ ያበረታቷቸው። በተቻለ መጠን ከአምስት ደቂቃ በላይ አይውሰዱ።

**4ኛ- አምስተኛውን የድራማ ክፍል ማጫወት (15 ደቂቃ)**

**ከድራማው ተቀንጭቦ የተወሰደ**
ብርሃኑ ባለበት ንጹሕ ዝር እንዳትል ተስፋ ያስጠነቅቃታል። በዚህ ጉዳይ ሊግባቡ አልቻሉም። ተስፋም ሰፈር ውስጥ በሚገኘው ጠላ ቤት ያመሻል፤ ንጹሕም በሰላም ይመለስ ይሆን ብላ ተጨንቃለች።

በሌላ በኩል የጊዜያዊው ድልድይ ግንባታ ተጠናቅቋል። ይሁን እንጂ ሰዎች ከባድ ጭነት ይዘው በጊዜያዊው ድልድይ ላይ መሻገራቸው በኮሚቴ አባላቱና በሌሎቹ የአካባቢው ነዋሪዎች መካከል ውጥረት ፈጥሯል።

**5ኛ፦ ውይይቱን መምራት (20 ደቂቃ)**

ተሳታፊዎች ወ/ሮ በለጤ፣ አቶ አማንና አቶ አያሌው ስለ ድልድዩ ያደረጉትን ውይይት እንዲያስታውሱ ያድርጉ፡፡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንድ በአንድ በመጠየቅ ውይይቱን ይምሩ፡፡ ውይይቱን በተመደበው ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ እንድትችሉ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከሚያስፈልገው ጊዜ በላይ አትውሰዱ፡፡

1. ወ/ሮ በለጤ፣ አቶ አማን እና አቶ አያሌው ሰዎች ከባድ ጭነት ይዘው በድልድዩ ላይ እንዳይሻገሩ የከለከሉት ለምንድን ነው?
2. እነዚህ ሦስት ሰዎች ለድልድዩ ትልቅ ቦታ የሚሰጡት ለምንድን ነው?
3. በምትኖሩበት አካባቢ ሰዎች የሚያጋጥማቸው አንዳንድ ችግሮች ምንድን ናቸው?
4. እነዚህን ችግሮች ለመወጣት ማኅበረሰቡ ምን ማድረግ ይችላል?
5. ሰዎች እነዚህን እርምጃዎች የማይወስዱት ለምንድን ነው?

**6ኛ፦ ዋና ዋና ሃሳቦችን በአጭሩ ማቅረብ (10 ደቂቃ)**

በውይይቱ ላይ የተነሱትን ቁልፍ ሃሳቦች ጨምቀው ያቅርቡ። ከዚህ በታች የተገለፁትን ነጥቦች በክለሳው ወቅት በሚገባ ማንሳትዎትን አይዘንጉ።

- በኅብረተሰቡ ውስጥ መፍትሄ ለመስጠት የጋራ ጥረት የሚጠይቁ ብዙ ችግሮች ያጋጥማሉ። ይሁን እንጂ ሰዎች በመፍትሄ ሐሳብ ላይ በአብዛኛው የተለያየ አመለካከት ስለሚኖራቸው ወደ ተግባር መግባት አስቸጋሪ ነው።
- ለችግሩ መፍትሄ ለመስጠት ወዲያውኑ ወደተግባር መግባት አስፈላጊ ነው። ለመፍትሄ አንዱ ሌላውን የሚጠብቅ ከሆነ ማኅበረሰቡ ችግሮቹን ይዞ ለመኖር ይገደዳል። እነዚህ ችግሮች በቆዩ መጠን ደግሞ ሌሎች ችግሮችን ይወልዳሉ።
- ስለዚህ ለመፍትሄው ቅድሚያውን ወስዶ መንቀሳቀስነው። ይህም የሁሉም ኃላፊነት ነው። ምንም እንኳ ሥራው ፈታኝ ቢሆንም የመጀመሪያው እርምጃ መወሰድ ያለበት አሁን ነው።
- በኅብረተሰቡ ውስጥ እንደ ወባ በሽታ፣ የእናቶች እና የሕፃናት ጤና ችግሮች፣ የግል እና የአካባቢ ንፅሕና ጉድለት እና የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ያሉ እክሎች ኅብረተሰቡ በጋራ እርምጃ እንዲወስድ ይጠይቃሉ። ቤተሰባችንንና ኅብረተሰባችንን ከበሽታ ማዳን እንድንችል ሁላችንም በእነዚህ አንገብጋቢ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት ለመጀመር የመጀመሪያውን እርምጃ መውሰድ አለብን።

**7ኛ፦ ቀላል የቤት ሥራ (3 ደቂቃ)**

በሚኖሩበት አካባቢ ማኅበረሰቡ የተደቀነበትን ችግርና ችግሩን ለማስወገድ ተሳታፊዎች ራሳቸው በአፋጣኝ ምን እርምጃ መውሰድ እንደሚችሉ እንዲያስቡ እና እንዲጽፉ ጠይቁ።

**8ኛ፦ ለአድማጮች ምስጋና ካቀረቡ በኋላ ስብሰባው ማብቃቱን ያሳውቁ**

# ክፍል 6
# በባል እና ሚስት መካከል ያለ የኃይል ሚዛን

**<u>ክፍሉ የሚወስደው የጊዜ ርዝመት በግምት</u>**

1 ሰዓት

**<u>የክፍሉ ዓላማ</u>**

ባልና ሚስት በሕይወታቸው (በልጅ አስተዳደግ፣ የጋራ ሃብትን እና ሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ) በጋራ ተማክረው እንዲወስኑ ለማበረታታት

**<u>የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች</u>**

ራዲዮ ድራማውን ለማጫወት የሚያስችል ማጫወቻ፣ ለቀኑ የተዘጋጀው የራዲዮ ድራማ ክፍል በፍላሽ ዲስክ ወይም በሲዲ፣ እስክርቢቶ፣ ማስታወሻ መያዣ ወረቀት

**1ኛ:- ሰላምታ ማቅረብ (2 ደቂቃ)**

**2ኛ:- ያለፈው ሳምንት ክለሳ (5 ደቂቃ)**

አድማጮች ባለፈው ሳምንት ከቀረበው ድራማ ምን እንደሚያስታውሱ ይጠይቁ፡፡ ተሳታፊዎቹ ከንጹሕና ከተስፋ ታሪክ እንዲሁም ከድልድዩ ግንባታ ጋር በተያያዘ የሚያስታውሱትን እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፡፡

ባለፈው ሳምንት የተሰጣቸውን የቤት ሥራ ሠርተው እንደሆነ ይጠይቋቸው፡፡

**3ኛ:- ዘና የሚያደርጉ ዝግጅቶች (5 ደቂቃ)**

ሴት ተሳታፊዎች ወንድ ቢሆኑ ኖሮ፤ ወንድ ተሳታፊዎችን ደግሞ ሴት ቢሆኑ ኖሮ በህይወታቸው ምን የተለየ ነገር ያደርጉ እንደነበር ጠይቋቸው፡፡ ይህንን አሁን እንዳያደርጉ ምን የሚያግዳቸው ነገር እንዳለ እንዲያብራሩ ዕድል ይስጧቸው፡፡ በተቻለ መጠን ከአምስት ደቂቃ በላይ አይውሰዱ፡፡

**4ኛ:- ስድስተኛውን ክፍል ድራማ ማጫወት (15 ደቂቃ)**

**ከድራማው ተቀንጭቦ የተወሰደ**

ተስፋ ሰክሮና በጣም አምሽቶ ወደ ቤት ይመጣል፡፡ በእንቅልፍ ልቡ የሌላ ሴት ስም ይጠራል፡፡ ንጹሕ ሁኔታው ያናድዳታል፡፡ ከዚህም ሌላ እሷን ሲያገባት የቤተሰቦቿን መሬት ለማረስ ቃል ገብቶ የነበረ ቢሆንም ቃሉን ባለማክበሩ ተናድዳለች፡፡ ተስፋም ቢሆን ንጹሕ የወሊድ መከላከያ እንደምትጠቀም ስለሚጠረጥር ይህ ጉዳይ ያበሳጨዋል፡፡

ድልድዩን ለማስገንባት የተቋቋመው ኮሚቴ ድልድዩን ቋሚ በሆነ መንገድ ለመሥራት ሳብረተሰቡ ገንዘብ እንዲያዋጣ ማሳመን ችሏል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ጊዜያዊው ድልድይ እንዳይበላሽ አጠቃቀሙን በተመለከተ ሕግ አውጥተዋል፡፡

**5ኛ:- ውይይቱን መምራት (25 ደቂቃ)**

ንጹሕ በተስፉ እንድትናደድ ያደረጓትን ሁለት ሁኔታዎች ማለትም ሰክሮ መምጣቱንና ተኝተው ሳለ የሌላ ሴት ስም መጥራቱን ለአድማጮች ያስታውሷቸው፡፡ ይህን ሁኔታ መጨረሻ ከቀረበው ትዕይንት ይኸውም ንጹሕ ባለማርገዟ ተስፉ መናደዱን ከሚያሳየው ጋር እያወዳደሩ ያቅርቡ፡፡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንድ በአንድ በመጠየቅ ውይይቱን ይምሩ፡፡ ውይይቱን በተመደበው ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ እንድትችሉ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከሚያስፈልገው ጊዜ በላይ አትውሰዱ፡፡

1. ተስፉ ሰክሮ በመምጣቱ ንጹሕ ስለሰጠችው ምላሽ ምን ይሰማችኋል?
2. በመጨረሻው ትዕይንት ተስፉ ስለሰጠው ምላሽ ምን ይሰማችኋል?
3. ከንጹሕና ከተስፉ በትዳራቸው ውስጥ ይበልጥ ተሰሚነት ያለው ማን ይመስላችኋል? ለምን?
4. በምትኖሩበት አካባቢ ከባሎች ወይም ከሚስቶች በቤተሰብ ጉዳዮች ዙሪያ ውሳኔ የሚወስነው ማን ይመስላችኋል?
5. ከባል እና ሚስት አንዱ ከሌላው ይበልጥ ተሰሚነት የሚኖረው ለምን ይመስላችኋል?
6. ቤተሰብን የሚመለከቱ ውሳኔዎች መወሰን የሚኖርባቸው እንዴት ነው? ለምን?
7. ሴቶችና ወንዶች እኩል የመወሰን መብት እንዲኖራቸው ምን መደረግ ይኖርበታል ትላላችሁ? በዚህ ረገድ ባልና ሚስቱ ምን ማድረግ ይችላሉ? ኅብረተሰቡስ ምን ማድረግ ይችላል?

**6ኛ፦ ዋና ዋና ሃሳቦችን በአጭሩ ማቅረብ (5 ደቂቃ)**

በውይይቱ ላይ የተነሱትን ቁልፍ ሃሳቦች ጨምቀው ያቅርቡ። ከዚህ በታች የተገለፁትን ነጥቦች በክለሳው ወቅት በሚገባ ማንሳትዎትን አይዘንጉ።

- የተሻሉ ውጤቶች እንዲገኙ በትዳር ውስጥ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች እኩል የመወሰን፤ በተለይ ቤተሰቡን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ መብት ሊኖራቸው ይገባል።
- ሴቶች የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን የበለጠ ስለሚገናኙ እና በአብዛኛው ልጆቻቸውን የሚንከባከቡት እነሱ ስለሆኑ በጤንነት ዙሪያ የተሻለ መረጃ ያላቸው እነሱ ሊሆኑ ይችላሉ።
- ባልና ሚስቶች የቤተሰቡን ጤንነት የሚጎዱ ነገሮችን በተመለከተ አንዳቸው የሌላውን እውቀት አቅልለው ሳይመለከቱ እርስ በርስ በግልጽ መነጋገር ይኖርባቸዋል።

**7ኛ፦ ቀላል የቤት ሥራ (3 ደቂቃ)**

ተሳታፊዎች ወደ ቤት ከተመለሱ በኋላ ቤተሰባቸውን የሚመለከት የጤና ጉዳይ አንስተው ከትዳር ጓደኛቸው ጋር ውይይት ማድረግ እንዲጀምሩ አድማጮችን ይጠይቋቸው።

**8ኛ፦ ለአድማጮች ምስጋና ካቀረቡ በኋላ ስብሰባው ማብቃቱን ያሳውቁ**

# ክፍል 7
# የተለምዶ ሕክምና

## ክፍሉ የሚወስደው የጊዜ ርዝመት በግምት

1 ሰዓት

## የክፍሉ ዓላማ

ሰዎች የወባ በሽታ ምልክቶችን ሲያዩ ጤና ኬላ/ጤና ጣቢያ በመሄድ የሕክምና እርዳታ ማግኘት እንደሚችሉ ማሳወቅና እንዲሄዱ ማነሳሳት

## የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች

ራዲዮ ድራማውን ለማጫወት የሚያስችል ማጫወቻ፣ ለቀኑ የተዘጋጀው የራዲዮ ድራማ ክፍል በፍላሽ ዲስክ ወይም በሲዲ፣ እስክርቢቶ፣ ማስታወሻ መያዣ ወረቀት

**1ኛ፦ ሰላምታ ማቅረብ (2 ደቂቃ)**

**2ኛ፦ ያለፈው ሳምንት ክለሳ (5 ደቂቃ)**

አድማጮች ባለፈው ሳምንት ከቀረበው ድራማ ምን እንደሚያስታውሱ ይጠይቁ፡፡ ተሳታፊዎቹ ከንጹሕና ከተስፋ ታሪክ እንዲሁም ከድልድዩ ግንባታ ጋር በተያያዘ ከተከሰተው ሁኔታ የሚያስታውሱትን ነገር እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፡፡

ባለፈው ሳምንት የተሰጣቸውን የቤት ሥራ ሠርተው እንደሆነ ይጠይቋቸው፡፡

**3ኛ፦ ዘና የሚያደርጉ ዝግጅቶች (5 ደቂቃ)**

ከተሳታፊዎች መካከል የወባ በሽታ ተይዞ የሚያውቅ ሰው ካለ ይጠይቁ፡፡ በታመሙበት ወቅት ምን ይሰማቸው እንደነበር ይጠይቋቸው፡፡ የታመመ ሰው ከሌለ የወባ በሽታ ምን ዓይነት ስሜት ይኖረዋል ብለው እንደሚገምቱ ተሳታፊዎችን ይጠይቁ፡፡ በተቻለ መጠን ከአምስት ደቂቃ በላይ አይውሰዱ፡፡

**4ኛ፦ ሰባተኛውን ክፍል ድራማ ማጫወት (15 ደቂቃ)**

**ከድራማው ተቀንጭቦ የተወሰደ**

ብርሃኑ ንጹሕን ለማየት ሲል ብቻ እየተከተላት ወደ ገበያ ይሄዳል፡፡ ከዚያም መነጋገር ጀመሩ፤ በመጨረሻም አብረው ተኙ፡፡ ብርሃኑ ወደ ቤት ሲሸኛት በድንገት ተስፋ አብረው ሲሄዱ ያያቸዋል፡፡ ተስፋ በንዴት በግኖ ንፁሕን ወደ ቤት ይዟት ይገባል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ኮሚቴው ድልድዩን ለመገንባት የገንዘብ እጥረት ያጋጥመዋል፡፡ ወ/ሮ በለጤን ጨምሮ አብዛኛው የማኅበረሰቡ ክፍል ገንዘብ አላዋጣም፤ ወ/ሮ በለጤ ትኩሳት ለያዛት ልጃቸው መድኃኒት እንዲሆናት የፍየል ወተት መግዣ ገንዘብ እያጠራቀሙ ስለሆነ ማዋጣት እንደማይችሉ ገልጸዋል፡፡ ደስ የሚለው ነገር በአካባቢው የሚኖር አንድ ነጋዴ የቀረውን ገንዘብ በማዋጣት ለችግሩ መፍትሄ ይሰጣል፡፡ ከዚህም ሌላ ነጋዴው መሐንዲስ የሆነው ልጁ የድልድዩን ግንባታ በነፃ እንዲቆጣጠር ፈቃደኛ መሆኑን ይገልጻል፡፡

**5ኛ፦ ውይይቱን መምራት (20 ደቂቃ)**

ወ/ሮ በለጤና ሌሎቹ የአካባቢው ነዋሪዎች ስለተነጋገሩት ጉዳይና በወቅቱ ወ/ሮ በለጤ ልጃቸው መታመሟን መግለጻቸውን አድማጮችን ያስታውሱ፡፡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንድ በአንድ በመጠየቅ ውይይቱን ይምሩ፡፡ ውይይቱን በተመደበው ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ እንድትችሉ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከሚያስፈልገው በላይ ጊዜ አትውሰዱ፡፡

1. የወ/ሮ በለጤ ልጅ ምን ችግር አጋጠማት?
2. ወ/ሮ በለጤ ልጃቸው እንዲሻላት ምን አደረጉ?
3. የወባ በሽታ ምልክቶች ምንድን ናቸው?
4. በአካባቢያችሁ የሚኖሩ አብዛኞቹ ሰዎች እነዚህን ምልክቶች ሲያዩ ምን ያደርጋሉ?
5. ምን ቢያደርጉ ኖሮ የተሻለ ይሆናል ትላላችሁ? ለምን?
6. እነዚህን ነገሮች የማያደርጉት ለምንድን ነው?

**6ኛ፦ ዋና ዋና ሃሳቦችን በአጭሩ ማቅረብ (10 ደቂቃ)**

በውይይቱ ላይ የተነሱትን ቁልፍ ሃሳቦች ጨምቀው ያቅርቡ። ከዚህ በታች የተገለፁትን ነጥቦች በክለሳው ወቅት ማንሳትዎትን አይዘንጉ።

- ብዙ በሽታዎች ህክምና ካልተደረገላቸው ለከፋ ሕመም ወይም የሞት ሊዳርጉ ይችላሉ። ይሁንና ተገቢውን ሕክምና በወቅቱ ከተደረገ ያለብዙ ስቃይ እና ወጪ ታማሚዎቹ ሊድኑ ይችላሉ።
- የጤና ባለሙያ የሚያዝዘውን መድኃኒት በአግባቡ መውሰድ ያስፈልጋል። ሕመሙ የተሻላችሁ ቢመስላችሁም እንኳን  መልሶ እንዳያገረሽባችሁ የታዘዘላችሁን መድሃኒት እስክትጨርሱ ድረስ ማቋረጥ የለባችሁም።
- ከማንኛውም በሽታ ለመዳን የሚያስፈልገውን ትክክለኛውን የመድኃኒት መጠን ማዘዝ የሚችለው የጤና ባለሙያ ነው። ስለዚህ የታዘዘላችሁን መድኃኒት በምንም ዓይነት ሁኔታ ለሌላ ሰው ማካፈል የለባችሁም።

**7ኛ፦ ቀላል የቤት ሥራ (3 ደቂቃ)**

ተሳታፊዎች የወባ በሽታ ምልክቶች ታይተውበታል ብለው የሚጠረጥሩትን አንድ ሰው አስታውሰው ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ ምክር እንዲሰጡት ይጠይቋቸው።

**8ኛ፦ ለአድማጮች ምስጋና ካቀረቡ በኋላ ስብሰባው ማብቃቱን ያሳውቁ**

# ክፍል 8
# ፆታዊ ጥቃት

**ክፍሉ የሚወስደው የጊዜ ርዝመት በግምት**

1 ሰዓት ከ 10 ደቂቃ

**የክፍሉ ዓላማ**

ፆታዊ ጥቃት በተለይ በባልና በሚስት መካከል ምን እንደሚያስከትል አድማጮች ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳደግ እና ይህን ጥቃት በመቃወም እርምጃ እንዲወስዱ ለማነሳሳት

**የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች**

ራዲዮ ድራማውን ለማጫወት የሚያስችል ማጫወቻ፣ ለቀኑ የተዘጋጀው የራዲዮ ድራማ ክፍል በፍላሽ ዲስክ ወይም በሲዲ፣ እስክርቢቶ፣ ማስታወሻ መያዣ ወረቀት

**1ኛ፦ ሰላምታ ማቅረብ (2 ደቂቃ)**

**2ኛ፦ ያለፈው ሳምንት ክለሳ (5 ደቂቃ)**

አድማጮች ባለፈው ሳምንት ከቀረበው ድራማ ምን እንደሚያስታውሱ ይጠይቁ፡፡ ተሳታፊዎቹ ከንጹሕና ከተስፋ ታሪክ እንዲሁም ከድልድዩ ግንባታ ጋር በተያያዘ ከተከሰተው ሁኔታ የሚያስታውሱትን ነገር እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፡፡

ባለፈው ሳምንት የተሰጣቸውን የቤት ሥራ ሠርተው እንደሆነ ይጠይቋቸው፡፡

**3ኛ፦ ዘና የሚያደርጉ ዝግጅቶች (5 ደቂቃ)**

አንድ ፈቃደኛ ተሳታፊ ከዚህ በፊት ከሰው ጋር አጋጥሟቸው ስለሚያውቅ አለመግባባት እንዲያስታውሱ እና የተፈጠረውን ሁኔታ ለቡድኑ እንዲያስረዱ ይጠይቁ፡፡ አለመግባባቱ እንዴት እንደተፈታ እንዳደናገሩ ይጠይቋቸው፡፡ ሌሎቹ ተሳታፊዎች እነርሱ ቢሆኑ ምን እንደሚያደርጉ ጠይቋቸው፡፡ በተቻለ መጠን ከአምስት ደቂቃ በላይ አይውሰዱ፡፡

**4ኛ፦ ስምንተኛውን ክፍል ድራማ ማጫወት (15 ደቂቃ)**

**ከድራማው ተቀንጭቦ የተወሰደ**

ተስፋ ንጹሕን ብርሃኑ ጋር ድርሽ እንዳትል ከነገራት በኋላ ከእሱ ጋር ስላያት ደበደባት፡፡ ሲደበድባት ስሜቱን መቆጣጠር ስላልቻለ በመጨረሻ ጥይቅ ተኮሰ፡፡ ንጹሕ እጅግ በመረበሿ በማታ አምልጣ ወደ እናቷ ሄደች፡፡

መሐንዲሱ ድልድዩን ለመገንባት የተገዙትን ቁሳቁሶች መስረቁ ከታወቀ በኋላ የአካባቢው ነዋሪ ኮሚቴውን በሙስና ይከሳል፡፡ ኮሚቴው መሐንዲሱን በማባረርና ለድልድዩ ግንባታ ገንዘብ ላዋጡት ነጋዴ አባቱ ጉዳዩን በማሳወቅ ሁኔታውን ያበርዳል፡፡

**5ኛ፦ ውይይቱን መምራት (30 ደቂቃ)**

ተስፋ ንጹሕን እንደደበደባት የሚያሳየውን የድራማውን የመጀመሪያ ትዕይንት ለአድማጮች ያስታውሱ። የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንድ በአንድ በመጠየቅ ውይይቱን ይምሩ። ውይይቱን በተመደበው ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ እንድትችሉ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከሚያስፈልገው በላይ ጊዜ አትውሰዱ።

1. ተስፋ ንጹሕን የደበደባት ለምንድን ነው?
2. እሷን ከመደብደብ ይልቅ ምን ሌሎች እርምጃዎች መውሰድ ይችል ነበር?
3. አንድ ባል ሚስቱን ለመደብደብ የሚያበቃው አጥጋቢ ምክንያት ምንድን ነው ትላላችሁ?
4. ወንዶች ሚስቶቻቸውን ምን ዓይነት ቅጣቶች ሊቀጡ ይችላሉ ትላላችሁ?
5. አንድ ባል በሚስቱ ላይ ማድረግ የለበትም የምትሏቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?
6. ባሎች በሚስቶቻቸው ላይ አካላዊ፣ ፆታዊ፣ ስሜታዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ማድረሳቸው ተቀባይነት ቢኖረው ኖሮ ምን ይፈጠር ነበር?
7. ወንዶች በሚስቶቻቸው ላይ አካላዊ፣ ፆታዊ፣ ስሜታዊና ኢኮኖሚያዊ በደል እንዲፈጽሙ የሚያስችሏቸው በማኅበረሰቦች ውስጥ ምን ዓይነት አመለካከቶች አሉ?
8. ባሎች ሲመቷቸው ወይም በሌሎች መንገዶች ጥቃት ሲፈጽሙባቸው ሴቶች ምን ማድረግ ይኖርባቸዋል?
9. በፆታ ላይ የተመሠረተ ጥቃትን ለማስቆም ማኅበረሰቡ ምን አይነት እርምጃዎች መውሰድ ይችላል?

**6ኛ፦ ዋና ዋና ሃሳቦችን በአጭሩ ማቅረብ (10 ደቂቃ)**

በውይይቱ ላይ የተነሱትን ቁልፍ ሃሳቦች ጨምቀው ያቅርቡ። ከዚህ በታች የተገለፁትን ነጥቦች በክለሳው ወቅት ማንሳትዎትን አይዘንጉ።

- ባሎች ሚስቶቻቸውን እንዲደበድቡ የሚያደርግ ምንም አጥጋቢ ምክንያት የለም። ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ስህተት ይፈጽማሉ፤ አለመግባባትም ይፈጠራል። ሆኖም ይህ ለወንዶች ወይም ለሴቶች የትዳር ጓደኛቸውን በምንም መልኩ "እንዲቀጡ" መብት አይሰጣቸውም።
- በፆታ ላይ የተመሠረት ጥቃት በአካል ላይ ብቻ የሚፈጸም አይደለም። መሳደብ፣ ማዋረድ፣ አስገድዶ የፆታ ግንኙነት መፈጸም፣ መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶችን መንፈግ፣ "ባሕላችንን አጉድፋችኋል" ወይም "የሴትነት ግዴታቸውን አልተወጡም" በሚል በሴቶች ላይ የሚፈጸም ቅጣት፣ ሴቶችን የመማር እድል እና ምግብ መከልከልን ሁሉ በፆታ ላይ የተመሠረቱ ጥቃቶች ናቸው።
- በፆታ ላይ የተመሠረት ጥቃት በቤተሰብ ጤንነት፣ ኢኮኖሚ እና አጠቃላይ ደኅንነት ላይ በርካታ ውስብስብ ችግሮች ያስከትላል። ልጆች በፆታ ላይ የተመሠረተ ጥቃት በማይፈጸምበት ቤት ውስጥ ሲያድጉ ይበልጥ ጤነኛ እና ንቁ አእምሮ ያላቸው ይሆናሉ።
- በሌላ በኩል ደግሞ በፆታ ላይ የተመሠረተ ጥቃት በሕግ የተከለከለ ነው፤ ወንጀልም ነው። ሴቶች ባሎቻቸው የሚደበድቧቸው ከሆነ ጉዳዩን ለፖሊስ በማሳወቅ ህጋዊ እርምጃ ችእንዲወሰድ ማድረግ ይችላሉ።
- ማንኛውም ሰው በትዳር ውስጥም ሆነ ከዚያ ውጪ ምንም ዓይነት በፆታ ላይ የተመሠረት ጥቃት ሲፈጸም አይቶ በቸልታ ካለፈ ችግሩ እንዲስፋፋ ያደርጋል። ሰዎች ጥቃት ሲፈጸም ካዩ መቼም ቢሆን ከመናገር ወደኋላ ማለት የለባቸውም።

**7ኛ፦ ቀላል የቤት ሥራ (3 ደቂቃ)**

ወንዶችም ሆኑ ሴቶች አድማጮችን በሳምንቱ ውስጥ ለትዳር ጓደኛቸው አንድ መልካም ነገር እንዲያደርጉ ይጠይቋቸው።

**8ኛ፦ ለአድማጮች ምስጋና ካቀረቡ በኋላ ስብሰባው ማብቃቱን ያሳውቁ**

## ክፍል 9
# የወባ በሽታ ሕክምና ማግኘት

**ክፍሉ የሚወስደው የጊዜ ርዝመት በግምት**

1 ሰዓት ከ 10 ደቂቃ

**የክፍሉ ዓላማ**

ሰዎች የወባ በሽታ ምልክቶችን ሲያዩ ጤና ተቋም በመሄድ የሕክምና እርዳታ ማግኘት እንደሚችሉ ለማሳወቅና እንዲሄዱ ለማነሳሳት

**የሚያስፈልጉ ቁሳ ቁሶች**

ራዲዮ ድራማውን ለማጫወት የሚያስችል ማጫወቻ፣ ለቀኑ የተዘጋጀው የራዲዮ ድራማ ክፍል በፍላሽ ዲስክ ወይም በሲዲ፣ እስክርቢቶ፣ ማስታወሻ መያዣ ወረቀት

**1ኛ- ሰላምታ ማቅረብ (2 ደቂቃ)**

**2ኛ- ያለፈው ሳምንት ክለሳ (5 ደቂቃ)**

አድማጮች ባለፈው ሳምንት ከቀረበው ድራማ ምን እንደሚያስታውሱ ይጠይቁ፡፡ ተሳታፊዎቹ ከንጹሕና ከተስፋ ታሪክ እንዲሁም ከድልድዩ ግንባታ ጋር በተያያዘ ከተከሰተው ሁኔታ የሚያስታውሱትን ነገር እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፡፡

ባለፈው ሳምንት የተሰጣቸውን የቤት ሥራ ሠርተው እንደሆነ ይጠይቋቸው፡፡

**3ኛ- ዘና የሚያደርጉ ዝግጅቶች (5 ደቂቃ)**

ተሳታፊዎች በሰባተኛው የድራማ ክፍል ላይ ስለወባ ከተነጋገሩት የሚያስታውሱትን ለቡድኑ እንዲያካፍሉ ጠይቋቸው፡፡ በተቻለ መጠን ከአምስት ደቂቃ በላይ አይውሰዱ፡፡

**4ኛ- ዘጠነኛውን ክፍል ድራማ ማጫወት (15 ደቂቃ)**

**ከድራማው ተቀንጭቦ የተወሰደ**

በአዲሱ መሐንዲስ ተቆጣጣሪነት የድልድዩ ግንባታ ቀጥሏል፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎች ኮሚቴው በሚያከናውነው ሥራ ደስተኞች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የወ/ሮ በለጤ ልጅ ጤና ጣቢያ ሳትሄድ በወባ በሽታ ሳቢያ በመሞቷ ማኅበረሰቡ ላይ የሐዘን ጥላ አጥልቷል፡፡

የንጹሕ እናትና ብርሃኑ፣ ተስፋ ንጹሕን እንደደበደበ በመስማታቸው እጅግ ተበሳጭተዋል፡፡ ብርሃኑ ከእሱ ጋር ወደ ከተማ እንድትኮበልል ንጹሕን ይጠይቃታል፡፡ ብዙም ደስ ሳይላት በጉዳዩ ትስማማለች፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተስፋ እሷን በመደብደቡ ጸጽቶታል፡፡ ልቧን መልሶ ለማግኘት ሲል የእሷን ቤተሰቦች እርሻ ማረስ ጀምሯል፡፡

**5ኛ፦ ውይይቱን መምራት (20 ደቂቃ)**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንድ በአንድ በመጠየቅ ውይይቱን ይምሩ። ውይይቱ በተመደበው ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ እንድትችሉ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከሚያስፈልገው በላይ ጊዜ አትውሰዱ።

1. በዚህ ድራማ ላይ ከቀረበው ውስጥ እጅግ አሳዛኝ የሆነው ሁኔታ ምንድን ነው? (አድማጮች የወ/ሮ በለጤ ሴት ልጅ ሞት ነው ወደሚል መደምደሚያ ላይ እንዲደርሱ ይምሯቸው)
2. የወ/ሮ በለጤ ልጅ የሞተችበት ምክንያት ምንድን ነው?
3. ሕይወቷን ለማትረፍ ምን ማድረግ ይቻል ነበር?
4. የወባ በሽታ ምልክቶች ምንድን ናቸው?
5. ሰዎች ትኩሳት ሲይዛቸው ምን ማድረግ ይኖርባቸዋል?

**6ኛ፦ ዋና ዋና ሃሳቦችን በአጭሩ ማቅረብ (10 ደቂቃ)**

በውይይቱ ላይ የተነሱትን ቁልፍ ነጥቦች ጨምቀው ያቅርቡ። ከዚህ በታች የተገለፁትን ነጥቦች በክለሳው ወቅት ማንሳትዎትን አይዘንጉ።

- የወባ በሽታ ሊድን የሚችል በሽታ ነው፤ ይሁንና አንድ ሰው ተገቢውን ሕክምና በወቅቱ ካላገኘ ለሞት ሊዳረግ ይችላል። የወባ በሽታ የያዘው ሰው ላይ መጀመሪያ ከሚታዩት ምልክቶች አንዱ ትኩሳት ነው። በመሆኑም አንድ ሰው ለ24 ሰዓት የማያቋርጥ ትኩሳት ከያዘው ወደ ጤና ተቋም መሄዱ የግድ አስፈላጊ ነው።
- ለወባ በሽታ የሚሰጠው የመድኃኒት መጠን ከሰው ወደ ሰው ሊለያይ ይችላል። ከበሽታው ለመዳን የሚያስፈልገውን ትክክለኛውን የመድኃኒት መጠን ማዘዝ የሚችለው የጤና ባለሙያ ነው። ስለዚህ የታዘዘላችሁን መድኃኒት በምንም ዓይነት ሁኔታ ለሌላ ሰው ማካፈል አይኖርባችሁም።
- መድኃኒቱን መውሰድ እንደጀመራችሁ ጤንነታችሁ እንደተሻሻለ ወዲያውኑ ይሰማችሁ ይሆናል፤ ይሁን እንጂ የታዘዘላችሁን መድኃኒት እስክትጨርሱ ድረስ መውሰድ አታቁሙ። መድኃኒቱን ሳትጨርሱ ካቆማችሁ በሽታው ሊያገረሽባችሁ ይችላል።

**7ኛ፦ ቀላል የቤት ሥራ (3 ደቂቃ)**

ተሳታፊዎቹ ዛሬ የተማሩትን ነገር ለቤተሰብ አባሎቻቸው እንዲያካፍሉ ይጠይቋቸው።

**8ኛ፦ ለአድማጮች ምስጋና ካቀረቡ በኋላ ስብሰባው ማብቃቱን ያሳውቁ**

## ክፍል 10
# አገበር መጠቀም

**ክፍሉ የሚወስደው የጊዜ ርዝመት በግምት**

1 ሰዓት ከ 10 ደቂቃ

**የክፍሉ ዓላማ**

አድማጮች አጎበርን በትክክልና በቋሚነት እንዲጠቀሙ ለማነሳሳት

**የሚያስፈልጉ ቁሳ ቁሶች**

ራዲዮ ድራማውን ለማጫወት የሚያስችል ማጫወቻ፣ ለቀኑ የተዘጋጀው የራዲዮ ድራማ ክፍል በፍላሽ ዲስክ ወይም በሲዲ፣ እስክርቢቶ፣ ማስታወሻ መያዣ ወረቀት

**1ኛ፦ ሰላምታ ማቅረብ (2 ደቂቃ)**

**2ኛ፦ ያለፈው ሳምንት ክለሳ (5 ደቂቃ)**

አድማጮች ባለፈው ሳምንት ከቀረበው የድራማ ክፍል ምን እንደሚያስታውሱ ይጠይቁ፡፡ ተሳታፊዎቹ ከንጹሕና ከተስፋ ታሪክ እንዲሁም ከድልድዩ ግንባታ ጋር በተያያዘ ከተከሰተው ሁኔታ የሚያስታውሱትን ነገር እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፡፡

ባለፈው ሳምንት የተሰጣቸውን የቤት ሥራ ሠርተው እንደሆነ ይጠይቋቸው፡፡

**3ኛ፦ ዘና የሚያደርጉ ዝግጅቶች (5 ደቂቃ)**

ተሳታፊዎችን የሚከተለውን እንቆቅልሽ ይጠይቋቸው፡፡

*ትንሽ ደቃቃ ባለክንፋም*
*የምትገድል በመሳም*

ተሳታፊዎች ለእንቆቅልሹ መልስ እንዲሰጡ ዕድል ይስጡ፡፡ በተቻለ መጠን ከአምስት ደቂቃ በላይ አይውሰዱ፡፡

**4ኛ፦ አስረኛውን ክፍል ድራማ ማጫወት (15 ደቂቃ)**

**ከድራማው ተቀንጭቦ የተወሰደ**

የንጹሕ እናትና የተስፋ እናት የወ/ሮ በለጤ ልጅ በመሞቷ ለቅሶ ሲደርሱ ይገናኛሉ፡፡ የንጹሕ እናት ለመቀበል ፈቃደኛ ባይሆኑም እንኳን የተስፋ እናት ልጃቸው ባደረገው ነገር አዝነው ይቅርታ ይጠይቃሉ፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ተስፋ ባለቤቱ ንጹሕ ጋር ሽማግሌዎች ይልካል፤ እነሱም ቤተሰቧን ይቅርታ ጠይቀው ይዘዋት ለመመለስ ቤተሰቧን ይማፀናሉ፡፡ ንጹሕ ትንሽ ካቅማማች በኋላ ወደ ባሏ ለመመለስ ትስማማለች፡፡ ስምምነት ላይ የደረሱት ንጹሕ ትምህርቷን እንደምትቀጥል፣ ከዚያ በፊት ግን ለባልዋ ልጅ እንደምትወልድለት ቅድመ ሁኔታዎች በማስቀመጥ ነው፡፡

**5ኛ፦ ውይይቱን መምራት (20 ደቂቃ)**

የዛሬው ድራማ በአብዛኛው በወ/ሮ በለጤ ልጅ ሞት ዙሪያ እንደሚያጠነጥን ለአድማጮች ያስታውሷቸው። የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንድ በአንድ በመጠየቅ ውይይቱን ይምሩ። ውይይቱን በተመደበው ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ እንድትችሉ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከሚያስፈልገው በላይ ጊዜ አትውሰዱ።

1. የትዝብት (የወ/ሮ በለጤ ልጅ) ሞት መንስኤ ምን ነበር? (የሞተቸው በወባ በሽታ ሳቢያ መሆኑን አድማጮች አለመዘንጋታቸውን ያረጋግጡ)
2. የወባ በሽታ ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፈው እንዴት ይመስላችኋል?
3. ሰዎች የወባ በሽታን ለመከላከል ምን ማድረግ ይችላሉ?
4. ሰዎች አሁን የጠቀሳችኋቸውን የመከላከያ እርምጃዎች የማይወስዱት ለምንድን ነው?
5. በምትኖሩበት አካባቢ ሰዎች አጎበር ማግኘት የሚችሉት ከየት ነው?
6. በምትኖሩበት አካባቢ ሰዎች አጎበር የማይጠቀሙት ለምንድን ነው?
7. ሰዎች አጎበር መጠቀም የሚኖርባቸው መቼ ነው?
8. አጎበር መስቀልና በአግባቡ መጠቀም የምትችሉት እንዴት ነው?

**6ኛ፦ ዋና ዋና ሃሳቦችን በአጭሩ ማቅረብ (10 ደቂቃ)**

በውይይቱ ላይ የተነሱትን ቁልፍ ሃሳቦች ጨምቀው ያቅርቡ። ከዚህ በታች የተገለፁትን ነጥቦች በክለሳው ወቅት ማንሳትዎትን አይዘንጉ።

- የወባ በሽታ ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፈው በወባ ትንኝ አማካኝነት ነው።
- አጎበር በትክክልና በቋሚነት መጠቀም በወባ በሽታ ላለመያዝ ይረዳል። አጎበር በመጠቀም የራሳችሁን፣ የቤተሰባችሁን እና በአጠቃላይ የማኅበረሰቡን ጤንነት መጠበቅ ትችላላችሁ።
- ወቅቱ የወባ በሽታ የሚከሰትበት ጊዜ ባይሆንም እንኳ ምንጊዜም አጎበር ተጠቀሙ።
- መንግሥት በቋሚነት አጎበር በነፃ ያድላል። በቂ አጎበሮች ከሌሏችሁ እርጉዝ ሴቶችና ከ5 ዓመት በታች ያሉ ልጆች በቅድሚያ እንዲያገኙ አድርጉ፤ ምክንያቱም ከሌላው ሰው ሁሉ ይልቅ ለወባ በሽታ ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑት እነሱ ናቸው።
- አጎበር ስትጠቀሙ ከፍራሹ ሥር በሚገባ ጠቅጥቃችሁ ማስያዛችሁን እርግጠኛ ሁኑ።

**7ኛ፦ ቀላል የቤት ሥራ (3 ደቂቃ)**

አድማጮች ከትዳር ጓደኛቸው እና ከሌሎች የቤተሰባቸው አባላት ጋር ስለ አጎበር አጠቃቀምና ቤታቸው ውስጥ በትክክል ስለመስቀል እንዲነጋገሩ ይጠይቋቸው።

**8ኛ፦ ለአድማጮች ምስጋና ካቀረቡ በኋላ ስብሰባው ማብቃቱን ያሳውቁ**

## ክፍል 11

# በቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ዙሪያ የተሳሳተ አመለካከት

**<u>ክፍሉ የሚወስደው የጊዜ ርዝመት በግምት</u>**

1 ሰዓት ከ 5 ደቂቃ

**<u>የክፍሉ ዓላማ</u>**

አድማጮች ስለ ቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ዙሪያ ያላቸውን ማንኛውንም አይነት የተሳሳተ አመለካከት አንስቶ ለመወያየት

**<u>የሚያስፈልጉ ቁሳ ቁሶች</u>**

ራዲዮ ድራማውን ለማጫወት የሚያስችል ማጫወቻ፣ ለቀኑ የተዘጋጀው የራዲዮ ድራማ ክፍል በፍላሽ ዲስክ ወይም በሲዲ፣ እስክርቢቶ፣ ማስታወሻ መያዣ ወረቀት

**1ኛ- ሰላምታ ማቅረብ (2 ደቂቃ)**

**2ኛ- ያለፈው ሳምንት ክለሳ (5 ደቂቃ)**

አድማጮች ባለፈው ሳምንት ከቀረበው ድራማ ምን እንደሚያስታውሱ ይጠይቁ፡፡ ተሳታፊዎቹ ከንጹሕና ከተስፋ ታሪክ እንዲሁም ከድልድዩ ግንባታ ጋር በተያያዘ ከተከሰተው ሁኔታ የሚያስታውሱትን ነገር እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፡፡

ባለፈው ሳምንት የተሰጣቸውን የቤት ሥራ ሠርተው እንደሆነ ይጠይቋቸው፡፡

**3ኛ- ዘና የሚያደርጉ ዝግጅቶች (5 ደቂቃ)**

"የሴት እና የማሰሮ ትንሽ የለውም" የሚለውን አባባል ተሳታፊዎች ያውቁት ከሆነ አባባሉ ምንን እንደሚያመላክት ይጠይቋቸው፡፡ አባባሉ ሴቶች ብዙ ልጆችን መውለድ እንደሚችሉ ወይም እንዳለባቸው ያሳያል፡፡ ይህ አባባል በህብረተሰቡ ውስጥ ምን ዓይነት ተፅዕኖ እንዳለው ተሳታፊዎች እንዲወያዩበት ያድርጉ፡፡ በተቻለ መጠን ከአምስት ደቂቃ በላይ አይውሰዱ፡፡

**4ኛ- አስራ አንደኛውን ክፍል ድራማ ማጫወት (15 ደቂቃ)**

**ከድራማው ተቀንጭቦ የተወሰደ**

ንጹሕ የወሊድ መቆጣጠሪያ መውሰድ አቁማለች፤ ይሁንና እስከ አሁን ድረስ ነፍሰ ጡር አይደለችም፡፡ ይህ ሁኔታ ያስጨነቃት በመሆኑ ከጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛ ጋር ተማክራለች፡፡ ቢሆንም ከባለቤትዋ ጋር ያላት ግንኙነት በጣም ተሻሽሏል፡፡

የድልድዩ ግንባታ የተጠናቀቀ ቢሆንም ወ/ሮ በለጤ ልጃቸው በመሞቷ ሃዘን ላይ ስለሆኑ እንዲሁም አቶ አያሌው ስላመማቸው የኮሚቴው አባላት የምርቃት በአል ማክበር አልቻሉም፡፡ ወቅቱ ወባ የሚከሰትበት ነው፡፡

**5ኛ፦ ውይይቱን መምራት (25 ደቂቃ)**

ንጹህ ማርገዝ ባለመቻሏ እርስዋ እና ተስፋ መጨነቃቸው በዚህ ክፍል ላይ መታየቱን አድማቾችን ያስታውሱ። የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንድ በአንድ በመጠየቅ ውይይቱን ይጨምሩ። ውይይቱን በተመደበው ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ እንድትችሉ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከሚያስፈልገው በላይ ጊዜ አትውሰዱ።

1. ተስፋና ንጹሕ ልጅ መውለድ አንችል ይሆናል ብለው የሰጉት ለምንድን ነው?
2. በእናንተ ባላችሁበት አካባቢ ያሉ ሰዎች ስለ ቤተሰብ እቅድ ዘዴዎች ምን ይሰማቸዋል?
3. ከቤተሰብ እቅድ ዘዴዎች ውስጥ የትኞቹን ታውቃላችሁ?
4. ሰዎች የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት መጠቀም ያለባቸው ለምንድን ነው?
5. ባላችሁበት ማኅበረሰብ ውስጥ ሰዎች የቤተሰብ እቅድ ዘዴዎችን መጠቀም የማይፈልጉባቸው ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?
6. ለጓደኞቻችሁና ለሌሎች ሰዎች ስለ ቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ምን ምክር ትሰጣላችሁ?

**6ኛ፦ ዋና ዋና ሃሳቦችን በአጭሩ ማቅረብ (10 ደቂቃ)**

በውይይቱ ላይ የተነሱትን ቁልፍ ሃሳቦች ጨምቀው ያቅርቡ። ከዚህ በታች የተገለፁትን ነጥቦች በክለሳው ወቅት ማንሳትዎትን አይዘንጉ።

- የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት እናቶች ከወሊድ በኋላ ጤናቸው እንዲመለስላቸው ይረዳቸዋል፣ ወላጆች ለልጆቻቸው በቂ ፍቅር ለማሳየትና ለመንከባከብ ያስችላቸዋል እንዲሁም ቤተሰብን በመደገፍ ረገድ የሚፈጠረውን ጫና እና ኃላፊነት ይቀንሳል።
- በርካታ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎቶች አሉ። የአጭር ጊዜ፣ የረጅም ጊዜ ወይንም ደግሞ ተጨማሪ ልጅ መውለድ ለማይፈልጉ የተዘጋጁ ቋሚ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎቶች አሉ። በጤና ባለሙያዎች በመታገዝ የሚፈልጉትን ዘዴ መምረጥ ትችላላችሁ።
- እያንዳንዱ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ጊዜያዊ የወር አበባ ኡደት መዛባትን የመሳሰሉ ቀላል የጎንዮሽ ችግሮች ሊያስከትል ይችላል። እነዚህ ችግሮች በቀላሉ ሊስተካከሉ የሚችሉ ሲሆን በአብዛኛውን ጊዜ በራሳቸው ይስተካከላሉ።
- ቋሚ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ካልሆነ በስተቀር ሁሉም ዘዴዎች መሃንነት ወይም ሌላ አይነት ጉዳት በሰውነት ላይ አያስከትሉም። በመረጣችሁበት ጊዜ ማርገዝ ትችላላችሁ።

**7ኛ፦ ቀላል የቤት ሥራ (3 ደቂቃ)**

የቤተሰብ እቅድ አገልግሎትን በተመለከተ በሳምንቱ ውስጥ ቢያንስ ከአንድ ሰው ጋር እንዲነጋገሩ ተሳታፊዎችን ይጠይቋቸው።

**8ኛ፦ ለአድማጮች ምስጋና ካቀረቡ በኋላ ስብሰባው ማብቃቱን ያሳውቁ**

ክፍል 12

# የቅድመ ወሊድ ክትትል ቶሎ መጀመር

**ክፍሉ የሚወስደው የጊዜ ርዝመት በግምት**

1 ሰዓት

**የክፍሉ ዓላማ**

ሴቶች ባረገዙ በመጀመሪያዎቹ ሦስት ወራት የቅድመ ወሊድ ክትትል ማድረግ እንዲጀምሩ ለማበረታታት

**የሚያስፈልጉ ቁሳ ቁሶች**

ራዲዮ ድራማውን ለማጫወት የሚያስችል ማጫወቻ፣ ለቀኑ የተዘጋጀው የራዲዮ ድራማ ክፍል በፍላሽ ዲስክ ወይም በሲዲ፣ እስክርቢቶ፣ ማስታወሻ መያዣ ወረቀት

**1ኛ፦ ሰላምታ ማቅረብ (2 ደቂቃ)**

**2ኛ፦ ያለፈው ሳምንት ክለሳ (5 ደቂቃ)**
አድማጮች ባለፈው ሳምንት ከቀረበው ድራማ ምን እንደሚያስታውሱ ይጠይቋቸው፡፡ ተሳታፊዎቹ ከንጹሕና ከተስፋ ታሪክ እንዲሁም ወ/ሮ በለጤ፣ አቶ አማንና አቶ አያሌው ምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ የሚያስታውሱትን ነገር እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፡፡

ባለፈው ሳምንት የተሰጣቸውን የቤት ሥራ ሠርተው እንደሆነ ይጠይቋቸው፡፡

**3ኛ፦ ዘና የሚያደርጉ ዝግጅቶች (5 ደቂቃ)**
ሴት ተሳታፊዎች በእርግዝናቸው ወቅት የከበዳቸው ነገር ካለ ይጠይቋቸው፡፡ ለችግሩ ምን መፍትሔ እንደሰጡ ለቡድኑ እንዲያካፍሉ ይጠይቋቸው፡፡ ወንድ ተሳታፊዎች ደግሞ ባለቤቶቻቸው ነፍሰ ጡር በነበሩበት ጊዜ ያሳስባቸው የነበረውን ጉዳይ ለቡድኑ እንዲያካፍሉ ይጠይቋቸው፡፡

**4ኛ፦ አስራ ሁለተኛውን ክፍል ድራማ ማጫወት (15 ደቂቃ)**

**ከድራማው ተቀንጭቦ የተወሰደ**
ንጹሕ እንዳረገዘች ጠርጥራለች፤ ተስፋ ደግሞ በሁኔታው እጅግ ፈንድቋል፡፡ ከጓደኛዋ ጋር ወደ ጤና ጣቢያ ሄዳ ማርገዟን አረጋግጣለች፡፡ ብርሃኑ እሷን ለማግኘት ወደ ጤና ጣቢያው ይሄዳል፤ ከዚያም ከምርመራ ክፍሉ ስትወጣ ያገኛታል፡፡ ከፊቷ ዞር እንዲልላት ለማድረግ ማርገዟን ትነግረዋለች፡፡

ተስፋ የንጹሕን የምርመራ ውጤት መጀመሪያ የሰማው ከብርሃኑ ነው፡፡ ንጹሕ ወደ ቤት ስትመለስ ተስፋ በመጀመሪያ ብስጭቱን በእሷ ላይ ይወጣል፡፡ በንዴት ቱግ ብሎ ጠመንጃውን ይዞ ከቤት ይወጣል፡፡

**5ኛ፦ ውይይቱን መምራት (20 ደቂቃ)**

በድራማው መጀመሪያ ላይ ንጹሕ ወደ ጤና ጣቢያ ለመሄድ እየተዘጋጀች እንደነበር፣ እዚያም ከደረሰች በኋላ ከጤና ባለሙያው ጋር መነጋገሯን ለአድማጮች ያስታውሷቸው። የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንድ በአንድ በመጠየቅ ውይይቱን ይምሩ። ውይይቱን በተመደበው ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ እንድትችሉ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከሚያስፈልገው በላይ ጊዜ አትውሰዱ።

1. ንጹሕ ወደ ጤና ጣቢያ የሄደችው ለምንድን ነው?
2. እናንተ በምትኖሩበት አካባቢ ሴቶች ማርገዛቸውን የሚያውቁበት የተለመደው መንገድ ምንድን ነው?
3. ሴቶች ማርገዛቸውን እንደጠረጠሩ ወዲያውኑ የቅድመ ወሊድ ክትትል ማድረጋቸው አስፈላጊነቱ ለምን ይመስላችኋል?
4. በምትኖሩበት አካባቢ ሴቶች እንዳረገዙ ሲጠረጥሩ ወዲያውኑ ወደ ጤና ጣቢያ እንዳይሄዱ የሚያግዳቸው ነገር ምንድን ነው?
5. አሁን የጠቀሳችኋቸውን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ለመወጣት ሴቶች ምን ማድረግ የሚችሉ ይመስላችኋል?
6. ሌሎች ሴቶች እንዳረገዙ ሲጠረጥሩ ወዲያውኑ የቅድመ ወሊድ ክትትል እንዲጀምሩ በማድረግ ረገድ እናንተ ምን አስተዋጽኦ ማበርከት ትችላላችሁ?

**6ኛ፦ ዋና ዋና ሃሳቦችን በአጭሩ ማቅረብ (10 ደቂቃ)**

በውይይቱ ላይ የተነሱትን ቁልፍ ሃሳቦች ጨምቀው ያቅርቡ። ከዚህ በታች የተገለፁትን ነጥቦች በከለሳው ወቅት ማንሳትዎትን አይዘንጉ።

- አንዴት ሴት እንደጸነሰች በምትጠረጥርበት ጊዜ በአቅራቢያዋ ወደሚገኝ የጤና ተቋም መሄድ ይኖርባታል። በተቋሙ የሚገኘው የሕክምና ባለሙያ መጸነሷን በእርግጠኝነት ለማወቅ ምርመራ ያደርግላታል።
- ወደ ጤና ተቋም በጊዜ ከሄዳችሁ (በመጀመሪያዎቹ ሦስት ወራት) ከእርግዝና ጋር ተያይዘው ለሚከሰቱ እንደ ማቅለሽለሽ ያሉ የጤና መታወኮች መፍትሄ ማግኘት ትችላላችሁ። በተጨማሪም ደም ማነስን ለመከላከል የሚረዳ አገልግሎት ማግኘት የምትችሉ ከመሆኑም ሌላ የእናንተንም ሆነ የጽንሱን ሕይወት ከአደጋ የሚያድን ክትባት ይሰጣችኋል። በሌላ በኩል ደግሞ አደገኛ የእርግዝና ምልክቶችን በተመለከተ ምክር ታገኛላችሁ፤ ይህም ሳይዘገይ እርምጃ እንድትወስዱ ያስችላችኋል።
- የመጀመሪያውን የቅድመ ወሊድ ክትትል አገልግሎት ከየትኛውም የጤና ማዕከል በነፃ ማግኘት ይቻላል። በመላው የእርግዝና ወቅት ቢያንስ 4 ጊዜ የቅድመ ወሊድ ክትትል ማድረግ ይኖርባችኋል። የጤና ባለሙያው ለቀጣዩ የቅድመ ወሊድ ክትትል መቼ እንደምትመጡ ቀጠሮ ይሰጣችኋል። ይህ ካልሆነ ራሳችሁ መጠየቅ አለባችሁ።
- የእርግዝና ክትትል ቀጠሮ እንዳያመልጣችሁ ተጠንቀቁ፤ ምክንያቱም ክትትሉ ለእናንተ ጤንነትም ሆነ ለጽንሱ ጤንነት የግድ አስፈላጊ ነው።

**7ኛ፦ ቀላል የቤት ሥራ (3 ደቂቃ)**

ተሳታፊዎች የእርግዝና ክትትል እንዳያደርጉ ወይም እንዲዘገዩ የሚያደርጋቸውን ችግር እንዲያስቡ እና እንዲፅፉ ይጠይቁ።

**8ኛ፦ ለአድማጮች ምስጋና ካቀረቡ በኋላ ስብሰባው ማብቃቱን ያሳውቁ**

This facilitation guide is made possible by the generous support of the American people through the United States Agency for International Development (USAID). The contents are the responsibility of Johns Hopkins Center for Communication Programs Ethiopia and do not necessarily reflect the views of USAID or the United States Government.